# ልዑል እግዚአብሔር፥

## በኢትዮጵያዊው ሥርዓት፣
## ጥር ፩ ቀን ለሚከበረው፣
## ለ፳፻፲ (፪ሺ፲)ኛው ዓመት፣
## የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ
## ጥምቀት፤ እንዲሁም፣
## ለተአምራዊው
## የቃና ዘገሊላ ሠርግ፥
## ለመድኃኒታችን ድንግል-ማርያም
## ሰማያዊ ፍልሰትና
## ለኪዳነ ምሕረት በዓላት፣
## እንኳን፣ በያለንበት፣
## በደኅንነትና በሰላም አደረሰን!

## የአምላካችንና የሰላማችን፥ የሊቀ-ካህናታችንና የንጉሠ-ነገሥታችን፡
## የኢየሱስ መሲሕ በዓለ ጥምቀት፤
## ሥርዓተ ጸሎት፤ ምንባባትና ምስባካት።

---

**የሥርዓተ-ጥምቀት።**

**ምንባብ፦**

**የሐዋርያት ሥራ፦** ምዕ. ፰፥ ቁ. ፳፯-፴፱።

**የሥርዓት ቅዳሴ።**

**የሐዋርያው፡ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት፡ ወደቲቶ፦** ምዕ. ፫፥ ቁ. ፫-፲፩።
**የሐዋርያው፡ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት፡ ፩ኛዪቱ፦** ምዕ. ፭፥ ቁ. ፭-፲፪።
**የሐዋርያት ሥራ፦** ምዕ. ፲፥ ቁ. ፴፬-፴፰።

**ምስባክ፤** **የሥርዓተ-ጥምቀት።**

**መዝ. ፻፲፫፥ ቁ. ፫-፬።**

ባሕርኒ፡ ርእየት፥ ወጐየት፤ ባሕር አየች፤ ሸሸችም፤
ወዮርዳኖስኒ፡ ገብአ ድኅሬሁ፤ ዮርዳኖስም፡ወደኋላው ተመለሰ፤
አድባር አንፈርዓፁ፡ ከመ ሓራጊት። ተራሮችም፡ እንደእንቦሳዎች ፈነደቁ።

**የሥርዓተ-ጥምቀት።**

**መዝ. ፻፲፫፥ ቁ. ፭-፮።**

ምንተ ኮንኪ ባሕር፡ ዘጐየይኪ? አንቺ ባሕር፡ የሸሸሽ፡ ምን ኾነሽ ነው?
ወአንተኒ ዮርዳኖስ፡ ዘገባእከ ድኅሬከ? አንተስ ዮርዳኖስ፡ ለምን፡ ወደኋላህ ተመለስህ?
አድባር፡ ዘአንፈርዓፅክሙ፡ ከመ ሓራጊት? ተራሮችስ፡ ለምን፡ እንደእንቦሳ ዘለላችሁ?

**ወንጌል፤** **የሥርዓተ-ጥምቀት።**

**የቅዱስ ሉቃስ፦** ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፳፫።

**የሥርዓተ-ጥምቀት።**

**የቅዱስ ማቴዎስ፦** ምዕ. ፫፥ ቁ. ፩-፲፯።

**ፍሬ ቅዳሴ**

**ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ።**

\+ \+ \+

## የበዓለ-ጥምቀት አጫጭር ወረቦች (የሽብሸባ ዝማሬዎች)

**፩.** ***ኀዲጎ ተስዓ፣ ወተስዓተ ነገደ!***
***ማእከለ ባሕር፥ ቆመ ማእከለ ባሕር!***

**ትርጉም**

ዘጠና ዘጠኙን (ነገደ-መላእክት)፡ በሰማያት ትቶ፣
የጠፋውን አንዱን (የአዳምንና የሔዋንን ነገድ) ሊፈልገው መጥቶ፣
ማግኘቱን ለፍጥረት፡ ባዋጅ አሳወቀ፤
በባሕር መካከል ቆሞ፡ ተጠመቀ።

**፪.** ***አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን!***
***መንክር፡ ስብሓተ ጥምቀቱ!***

**ትርጉም**

ዕፁብ ነው! ድንቅ ነው! በእውነት፡ በእውነት! (፪ ጊዜያት)
የእግዚአብሔር ወልድ ጥምቀት፡ ኾነ በሰውነት፡ (፪ ጊዜያት)

## የምሥራች ሰላምታ

በዚህ በዓልና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ እስከአስተርእዮ ማርያም ድረስ፡
ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡
በንግግርና በዜማ፡ እርስ በርሳቸው፤ የሚለዋወጡት የምሥራች ቃል፡-

**"ተፈጸመ ጥምቀት፡ ዘመሲሕ-ኢየሱስ!"**
**"በፈለገ-ዮርዳኖስ፣ በእደ-ዮሐንስ!"**

ማለትም፡ "ጥምቀት ተፈጸመ፡ የመሲሕ-ኢየሱስ!"
"እጁ፡ የዮሓንስ፣ ወንዙ፡ የዮርዳኖስ!"

እንዲሁም፡ **"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"**
**በእንተ ጥምቀቱ፡ ለእግዚእነ፥ ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ!"**

ማለትም፡ "ዛሬ፡ ታላቅ ደስታ ኾነ!
እግዚአብሔራችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ተጠምቋልና!"

# መግቢያ

የእናቲቱ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ በዓላተ-ትስብእት፡ በእርሱ፡ በታኅሣሥ ፩ዱ ቀን ተጀምሮ፡ በእርሷው፡ በታኅሣሥ ፯ቱ ቀን በኩልም ዐልፎ፣ የረቡዕና የዓርብ ጾምም እንኳ ሳይኖርበት፡ በፍጹሙ የጾመ-ማርያምነት መንፈሳዊ ደረጃ እየተካኼደ፡ "ከተራ" እስከሚባለው፣ በአንዲት ቀን የጋድ ጾም እስከሚዘከረው፡ እስከጥምቀት ዋዜማ ቀጥሎ፡ በታኅሣሥ ፴ ቀን ያበቃል።

በማግሥቱም፡ ጥር ፩ ቀን የሚውለው፡ ታላቁ፡ የፈጣሪያችንና የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕ በዓለ-ጥምቀትና ዘመነ-አስተርእዮው፡ ጥር ፯ ቀን በሚታሰበው፡ በቅድስት ሥላሴ በዓል ቀጥሎ፣ ከዚያም፡ ጥር ፲፪ ቀን በሚታወሰው፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ መታሰቢያ፣ ተያይዞም፡ ጥር ፳፩ ቀን በሚዘከረው፡ በመድኃኒታችንና እናታችን፣ አገራችንና ንግሥታችን፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ሰማያዊ ፍልሰት፡ እነዚህን ኹሉ በዓላት ዐልፎ፡ በመጨረሻ፡ <u>ከጥር ፳፰ እስከ ፴ ቀን ድረስ፡</u> **ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በታላቅ ድምቀት በሚካኼደው፡ በዓለ-ኢትዮጵያ፡** የረቡዕና የዓርብ ጾምም በሌለበት፣ የፋሲካ ደረጃ፡ በከፍተኛ የሐሤት መንፈስ ይከበራል።

ከዚህ፡ የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ ከኾነው በዓለ-ጥምቀት ተነሥቶ፡ ከላይ የተጠቀሱትን በዓላት በማካተት፡ የኪዳነ-ምሕረት፡ ዓመታዊ በዓለ-ዝክር እስከሚውልበት፡ እስከየካቲት ፲፮ ቀን ድረስ፡ ባሉት ወራትና ሳምንታት ውስጥ ስለሚከበሩት በዓላት፡ የሚከተለውን ማብራሪያ አቅርበንላችኋል።

## ዘመነ አስተርእዮ።

"አስተርእዮ"፡ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ፡ "አስተርእዮ ማርያም" እየተባለ፡ በዘልማድ እንደሚነገረው አባባል፡ በበዓላት ላይ እየተቀጸለ የሚደመጥ ዘይቤ አለ፤ ግን፡ እንዲህ የሚባለው፡ ለምን እንደኾነ፡ ልናውቀው ይገባል።

"አስተርእዮ"፡ "ታየ፤ ተገለጠ" የሚል ትርጉም ካለው፡ "ተርእየ" ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው፤ "በገሃድ መታየት"፥ "በይፋ መገለጥ" ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ከበዓለ-ጥምቀት አንሥቶ፡ እስከ**በዓለ-ኢትዮጵያ** (እስከቀድሞው ጾመ-ኢትዮጵያ=ጾመ-ነነዌ) ድረስ፡ ያለው ጊዜ፡ "ዘመነ-አስተርእዮ" ይባላል። እንዲህ የተባለበትንም ምክንያት፡ ከዚህ የሚከተለው ሓተታ ያብራራዋል፡-

**አስተርእዮ፡** "የዲያብሎስን የክፋት አገዛዝ፣ የኃጢአትን [የሓሰትን] ቀንበር እና የሞትን የማይቀር ፍዳ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ በመደምሰስ፡ ፍጥረቱን ኹሉ ለማዳን፡ ወደምድራዊው ዓለም ይመጣል!" ተብሎ፡ ትንቢት ተነግሮለትና ሱባኤ ተቆጥሮለት፡ በተስፋ የተጠበቀው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ፍጹም ሰው በመኾን፡ እግዚአብሔር እም፡ አስቀድማ በተዋሓደቻት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ያለሰብአዊ ወንድ ዘር ተፀነሰ፤ ከእርሷም፡ በድንግልና ተወልዶ፡ "ወልደ-ዕጓለ-እመሕያው" = "የማርያም ልጅ" ተባለ። ከኃጢአት በቀር፣ በኀውን፡ የሰውን ሥራ እየሠራም፡ ለሠላሳ ዘመን፡ በምድር ላይ ተመላለሰ።

"ከዚህ በኋላ፡ በመለኮትነትና በሰውነት የወለደችው እናቱ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ በአካለ ሥጋ፡ አጠገቡ እያለች፣ በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ቆሞ ሣለ፡ አባቱ እግዚአብሔር አብ፡ ድምፁን፡ ከደመና በማሰማት፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ በርግብ አምሳል፡ ከሰማያት ወርዶ፡ ራሱ ላይ በመቀመጥ፣ እርሱ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ወልድም፡ በዐዋጅ ነጋሪው፡ በዮሓንስ እጅ በመጠመቅ፡ ማንነቱን፡ በይፋ ገለጠ።

ለዚህ ነው፡ በበዓሉ ዕለት፡ በዚያ፡ በባሕረ-ጥምቀቱ የማሕሌት ዐውድ [አደባባይ] ላይ፡ ካህናቱ፡ **"መጽአ ቃል፡ እምደመና፡ እንዘ ይብል፡- 'ዝንቱ፡ ውእቱ ወልድየ! ዘአፈቅር፣ ሎቱ ስምዕዎ!'**

"ከሰማይ፣ ከደመና፣ እንዲህ የሚል ቃል መጣ፡- 'ይህ፡ በመጥምቁ በዮሓንስ እጅ፣ በዮርዳኖስ ውኃ ሲጠመቅ የምታዩት፣ የምወድደው አንድ ልጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ነውና፡ እርሱን ስሙት!'" የሚለውን ወረብ አለዝበው፡ በከፍተኛ ኹለንተናዊ ሓሤት የሚያሸበሽቡት።

ይህ የጥምቀት ወራት፡ የማይታየው፡ የአምላክ አካልና ባሕርይ፣ ከሚታየው፡ የሰው አካልና ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ፡ የተገለጠበት ማንነቱ፡ በገሃድ የታወቀበትን ምስጢር በማብራራት፡ ምሥራቹ የሚነገርበት፣ በዚህ መለኮታዊ የቸርነት ድርጊትም፡ ሰው ኹሉ፡ ደስታውን የሚፈጽምበትና ምስጋናውን፡ ለፈጣሪው የሚያቀርብበት ጊዜ ስለኾነ፡ "ዘመነ አስተርእዮ" መባሉ፡ ትክክልና ተገቢ ኾኖ ይገኛል። *"ለጥምቀት የማይኾን ቀሚስ፣ ይበጣጠስ!"* የሚለውም፡ ሕዝባዊ የአነጋገር ዘዬ፡ ይህንኑ እውነታ ያመላክታል።

ጥምቀትና ከጥምቀት ጋር፣ ከእርሱም በኋላ፡ በዚሁ፡ በዘመነ አስተርእዮ፡ የሚከበሩት በዓላት፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

## በዓለ ጥምቀት።

ጥምቀት፡ በክርስቲያኑ ዓለም ካሉ ሕዝቦች ኹሉ ተለይቶ፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ብቻ፡ በታላቅ ድምቀት ይከበራል። የዚህንም ምክንያት ማወቁ፡ ለእየራሳችን ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎችም ለማስረዳት፡ ይጠቅማል፤ ያስፈልጋልም።

ምክንያቱ፡ እንዲህ ነው፡- በዘመነ-አስተርእዮ፡ ከሚከበሩት በዓላት መካከል፡ ዋናው፡ እንደምታውቁት፡ "ጥምቀት" ነው። የእርሱም፡ ዓመታዊ መታሰቢያው፡ ጥር ፲፩ ቀን የሚውል ኾኖ፡ "ከተራ" ከሚባለው፡ ከዋዜማው፡ ከታኅሣሥ ፳፱ ቀን ጀምሮ፡ በታላቅ ድምቀት ይከበራል። በዓሉ፡ በዚህ መልክ እንዲደራጅና እንዲዘከር የኾነው፡ በተዋሕዶ የከበረው፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ ፍጹም አምላክነት እና ፍጹም ሰውነት፡ ለዓለሙ ተገልጦ የተመሰከረበት ታላቅ ቀን በመኾኑ ነው።

ለበዓሉ ሥርዓት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን ባሕረ-ጥምቀት፡ ውኃውን፡ ከወንዝ፡ በቦይ መርተውና ከትረው (ገድበው) የሚያዘጋጁበት፣ ለመንበረ-ታቦቱ ማሳረፊያና ለቀዳስያኑ ማገልገያ፣ ለደባትሩም፡ ማሕሌት መቆሚያና ለምእመናኑ መሰባሰቢያ የሚኾኑት ድንኳኖች የሚተከሉበት፣ በዚያ፡ በባሕረ ጥምቀቱ አካባቢ የሚያድረውም ሰው፡ በየወገኑ፡ የየራሱን ዳስ የሚቀልስበት ዕለት ስለኾነ፡ ይህ፡ የጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ "ከተራ" ተብሏል፤ እርሱም፡ "መከተር" (ውኃ መገደብ) ከሚለው ቃል የወጣ ነው።

በዘመነ ኦሪት፡ እስራኤል፡ ከግብፅ ከወጡ በኋላ፡ "ምድረ-ርስት" ወደተባለችው፡ የከነዓን አገር ከመግባታቸው በፊት፡ አርባ ዓመታት ሙሉ፡ በሲና ምድረ-በዳ ሲንከራተቱ፡ ማደሪያቸው፡ ድንኳንና ዳስ ስለነበረ፡ የኋላ ትውልድ፡ ያን፡ የመከራና የፈተና ዘመን እንዳይረሳ፡ "የዳስ በዓል" እያሉ፡ በየዓመቱ እንዲያከብሩት፡ እግዚአብሔር አዝዟቸው ነበረ።

እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኪዳነ-ኦሪቱ የብሉዩ ዘመን፡ በዚያው፡ በኦሪቱ ሥርዓት፡ ስናከብረው ከቆየን በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በዘመነ ክርስትና፡ በጥምቀት ተክተን፡ በዓሉን፡ እነሆ፡ ዛሬ በሚታሰብበት መልክ፡ ማክበራችንን ቀጠልን።

ስለዚህ፡ ካህናቱ፡ በልዩ ልዩ የጌጣጌጥ ጥልፍ፡ በተንቈጠቈጠ መጐናፀፊያ ተሸክመው፡ በዝግታ እየተራመዱ፡ በክብር የሚያጓጕዙት፡ የአዲስ ኪዳኑ ታቦት፡ በተለያዩ ቀለማት ባሸበረቁ፡ የተዋቡ አልባሳተ-ተክህኖ በተሸለሙ፣ የጧፍ መብራትንና ባለመያር መስቀልን፥ የማዕጠንተ-ወርቅ ጽንሓን፥ በሓርና በግምጃ፥ በከፈይም የተጌጡ ዣንጥላንና ድባብን በያዙ ልኡካን ተከብቦ፥ በማሕሌታውያኑ ደባትር ሃሌታ፣ በወጣት መዘምራን የውዳሴ ዜማና የፍሥሓ ዝማሬ፣ በወንዶች ሆታና በሴቶች እልልታ ታጅቦ፡ በበዓሉ ዋዜማ፡ ከቤተ-መቅደሱ ይነሣል።

በዚህ መልክ፡ ታቦቱ፡ ወደባሕረ-ጥምቀቱ ወንዝ፥ ወይም፡ ወደከተራው ቦታ ይወርድና በዚያው ዐድሮ፡ በማግሥቱ፡ በዋናው፡ የጥምቀት በዓል ዕለት፡ በታላቅ ብሔራዊና ሕዝባዊ፥ ምልክናዊና ገናናዊ፥ ክህነታዊና አርያማዊ ክብር፡ ወደመካነ መቅደሱ ይመለሳል። ለዚህ ሥርዓታችን፡ መነሻ የኾነውን ምክንያት፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት እናጠቃልልላችኋለን፡-

እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በጥምቀት በዓል የምናካኺደው ሥርዓት፡ እግዚአብሔር፡ ለእስራኤል ልጆች፡ "አወርሳችኋለሁ!" ብሎ፡ ተስፋ ወደሰጣቸው ምድረ-ርስት ይገቡ ዘንድ፡ የኢየሱስ መሲሕና የድንግል ማርያም፡ ቀዳሚት አርአያ የኾነችውን፡ ታቦተ-ጽዮንን፡ የአሪቱ ካህናት ተሸክመው፡ የዮርዳኖስን ወንዝ እንዲያቋርጡ፡ ትእዛዝ ሰጥቷቸው፡ ወንዙን ሲሻገሩ፡ የወንዙ ውኃ፡ ከኹለት ተከፍሎና በራሱ ኃይል ተከትሮ፡ ቆሞላቸው፡ ሕዝቡ፡ በኢትዮጵያ ቀይ ባሕር በኾነው ዓይነት፡ በደረቁ መሬት ለመሻገር የቻሉበትን፡ የእግዚአብሔርን ቸርነት ያስታውሰናል።

እንደዚያኑ ጊዜ ኹሉ፡ ዛሬ፡ በዘመነ-ሓዲስ ደግሞ፡ አማናዊቷ፥ ሕያውቷና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ-ጽዮን ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው፡ አማናዊው፥ ሕያዉውና ዘለዓለማዊው ጽላተ-ኪዳን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ፡ በመጥምቁ ዮሓንስ እጅ፡ ከተጠመቀ በኋላ፡ በእርሱ ጥምቀት፡ በእየራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ፡ እየራሳቸውን፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት አውጥተው፡ ለክፉው የዳረጉትን የሰው ወገኖች ኹሉ፣ በተለይም፡ አይሁድን፡ ከዲያብሎስ የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ አውጥቶ፡ እንደእኛ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር፡ እንዲቀዳጁ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ከኃጢኣት፡ ወደጽድቅ፣ ማለትም፡ ከሓሰት፡ ወደእውነት እና ከሞት፡ ወደሕይወት ተሻግረው፡ ዘለዓለማዊቷን የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረስ እንዲችሉ፡ የመጨረሻውን ዕድል ያቀዳጃቸው መኾኑን ያረጋግጥልናል።

"ተመልከት ዓላማህን! ተከተል አለቃህን!" በሚለው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መርሖ መሠረት፡-

-የቤተ-ምልክናው ሠራዊት፡ ከታቦቱ ፊት፡ "**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!** ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!" ደግሞም፡ "**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!** ከይሁዳ ነገድ የተወለደው አንበሳ፡ ድል አደረገ" የሚለው መለኮታዊ ማኅተም፡ በመኻከሉ የሠፈረበትን፡ የባለመዖር መስቀል ሰንደቅ-ዓላማውን አንግቦ፥ በገናና መሰንቆውን፥ እንቢልታና መለከቱን፥ ክራሩንና ጥሩንባውን፥ ልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያውን እየቃኘና የዜማ ድምፁን እያሰማ ይቀድማል፤

- የቤተ-ክህነቱ ዘርፍ የኾኑት ደባትሩና መዘምራኑ: በመካከሉ ቀጥለው፡ በመቋሚያና በጸናጽል፥ በከበሮና በጽፋት በደመቀ ማሕሌት እያሸበሸቡ ይጓዛሉ። ከታቦቱም በኋላ፡ የቤተ-ክህነቱ፥ የቤተ-ምልክናውና የቤተ-ሕዝቡ ባለሥልጣኖች፡ ታቦቱን፡ በታላቅ ፍቅርና ትሕትና፣ ክብርና ጽሙና ያጅባሉ።

-የቤተ-ሕዝቡ ወገን የኾነው፡ ወንዱም፡ ሴቱም፥ ሕፃኑም፡ ሽማግሌውም፡ ፀዓዳ (የጸዳ ነጫጭ) የክት ልብሱን ለብሶ፡ ከዚያ፡ በመጨረሻ፡ በሆታና በጭፈራ፣ በዘፈንና በእልልታ ይከተላል።

ይህም የሚኾነው፡ ከኪዳነ-ልቦናው ዘመን ጀምሮ፡ ሲሠራበት ከቆየው፡ ከጥንታዊው ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ጋር ተዋሕዶ የቀጠለውን፡ የመካከለኛውን፡ የኪዳነ ኦሪቱንና የመጨረሻውን፡ የኪዳነ-ምሕረቱን ዘመናት ሥርዓት ለማስታወስ ያህል ነው። እርሱዉም፡ እስራኤላዊው ኦሪታዊ ንጉሥ ዳዊት፡ ታቦተ-ጽዮን፡ በእስራኤል ካህናትና ሕዝብ ተረስታ፥ ተጥላም ከነበረችበት ሥፍራ፡ ወደኢየሩሳሌም ከተማ፡ በዐጀብ አምጥቶ፡ ባዘጋጀላት የማረፊያዋ ድንኳን ውስጥ፡ ባስገባት ጊዜ፡ ከከብት እረኝነት አንሥቶ፡ ለሕዝብ መሪነት ባበቃው ፈጣሪው ፊት፡ ከደስታው ብዛት የተነሣ፡ ራሱ፡ በካህናቱና በሕዝቡ ፊት፡ ዐብሮ እየዘመረና እያሸበሸበ፥ እየዘለለና እየጨፈረ፡ የምስጋና መባኡን ያቀረበበትን፥ የአምልኮ ፍቅሩንም የገለጸበትን ባህል የመሰለው መኾኑ ነው።

## ጥምቀት፡ የጥሙቃንም፡ የየግላቸው በዓል ስለመኾኑ።

የጥምቀት በዓል፡ የጌታችንና የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ በዓል ብቻ አይደለም፤ የእኛ፡ የባለአደራዎቹ፡ የኢትዮጵያ ልጆች በዓል ብቻም አይደለም፤ በእርሱ ጥምቀት ተቀድሰውና ተጠምቀው፡ የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን የበቁት፡ ያመኑት ብቻም አይደለም። በክፋትና በሓሰት፣ በክህደትና በዓመፅ የጠፉት፡ የአይሁድም፥ በጣዖት አምልኮ ተጠምደው ያላመኑት፡ የአሕዛብም፣ በጠቅላላም፡ የኹላችን፡ የሰው ልጆች በዓል ጭምር ነው እንጂ።

አዎን! በዓሉ፡ በመጀመሪያ ነገር፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በአዲሱ ኪዳን፡ የራሱን ማንነት፡ ለዓለም የገለጸባትንና ያስመሰከረባትን፡ ጥምቀቱንና ቀኂቱን ያስታውሰናል፤

ቀጥሎ፡ የኹሉ ፈጣሪና አምላክ የኾነው እርሱ፡ የተጠመቀው፡ **ለእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ በማሕፀን ለተጠመቅነው፥ ከዚያች፡ በማሕፀን ከተጠመቅንባት ቅጽበት ጀምሮም፡ ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ለኾንነው፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት ሳይኾን፡** ከኢትዮጵያዋ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ ተወልዶ፡ በተለይ፡ በቃል ኪዳን አፍራሽነታቸው ለጠፉት፡ ለአይሁድ በመኾኑ፡ እንዲህ፡ እነርሱን ያዳነበትን፥ ለእነርሱም፡ አብነትና አርአያ ያደረገውን፡ የጥምቀትን ሥርዓት፡ ራሱ ፈጽሞ፡ እነርሱም፡ ያንኑ ሥርዓት በመፈጸም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ተቀብለው፡ የእግዚአብሔር ልጆች ለመኾን እንዲበቁ የሚያስችላቸውን፡ አምላካዊ ፍቅርና ቸርነት፡ ያበረከተላቸው፥ የዕድል በሩንም የከፈተላቸው መኾኑን፥ ከዚህ የተነሣም፡ በእነርሱ ምክንያት፡ የሰው ወገን ኹሉ ጭምር የተቀዳጀውን፡ ይህን፡ ወደር የሌለውን፤ ዘለዓለማዊና የመጨረሻ ክብር፡ አጕልቶ ያሳየናል።

ይህን፡ ከዚህ በላይ የተገለጸውን እውነታ፡ እሙንነቱንና ትክክለኛነቱን፡ እንዲህ የሚለው፡ የመለኮታዊው መምህራችን፡ የኢየሱስ መሲሕ ቍርጥ ቃል ያረጋግጠዋል፡- "**ኢተፈነውኩ፡ ዘእንበለ ኀበ አባግዕ፡ ዘተሐጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል! ...ውስተ ፍኖተ-አሕዛብ፡ ኢትሑሩ! ወሀገረ ሳምር፡ ኢትባኡ! ወሑሩ ባሕቱ፤ ኀበ አባግዕ፡ ዘተኀጕላ፤ ዘቤተ-እስራኤል!**

"[እኔ] ከእስራኤል ወገን ወደኾኑት፡ ወደጠፉት በጎች ብቻ እንጂ፡ ወደሌላ አልተላክሁም! ...[እናንተም] ወደአሕዛብ የሚያደርሰውን መንገድ ይዛችሁ አትኺዱ! ወደሳምራውያን ከተማም እንኳ አትግቡ! ነገር ግን፡ ወደጠፉት፡ ወደእስራኤል ቤት በጎች ኺዱ እንጂ!" (ማቴ. ፲፥ ፭-፮፤ ፲፭፥ ፳፬።)

በዚሁ፡ በጥምቀት ረገድ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ አጽንተውና ቋሚ አድርገው ያኖሩትን፡ እግዚአብሔራዊ ጸጋቸውንና ይዞታቸውን፡ እዚህ ላይ አስተካክሎ ማዘከርና አቃንቶ ማሳወቅ፡ አግባብ ይኾናል። ይኸውም፡ በአንድ ወገን፡ ከሕገ-ልቦና አምልኳቸው ወጥተው፤ በጣዖት አምልኮ የጥፋት ዐዘቅት ውስጥ ከመውደቃቸው የተነሣ፡ እጅግ በጽኑ ይማቅቁ የነበሩትን፡ አረማውያንንና አሕዛብን፤ ይልቁንም፡ በሃይማኖት ከሃዲነታቸውና በቃል ኪዳን አፍራሽነታቸው፤ በክፉ አድራጊነታቸውና በሰይጣናዊው ዓመፀኝነታቸው ምክንያት፡ ከሕገ ኦሪቱ አምልኳቸው እንኳ ሳይቀር፡ ፈጽመው ስተው፡ በገሃድ የጠፉትን፡ አይሁድን፡ አጋልጦ የሚያቀርበው እውነታ ነው።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ በውኃ የኾነው፡ የመጥምቁ ዮሓንስ፡ የንስሓ ጥምቀት፣ ይልቁንም፡ ወሰንና መጠን፥ ወደርና መሰል በሌለው የፈጣሪ ቸርነት፡ ተከታትሎ፡ በመንፈስና በእሳት የኾነው፡ እውነተኛው የኢየሱስ መሲሕ ጥምቀት፡ በዚያን ጊዜ፡ ቀርቦላቸውና ተደርጎላቸው የነበረው፣ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዛሬ፣ ዛሬም እየኾነ ያለው፡ ለእነዚህ፡ ለኹለቱም ወገኖች [ለአይሁድና ለአሕዛብ] ብቻ መኾኑን የሚያመለክተው የዚሁ እውነታ፡ አንዱ ገጽታው ነው።

ከዚህ የተነሣ፥ ቀደም ብሎ፡ በተጠቀሰው፡ የመምህራችን የኢየሱስ መሲሕ ቃል መሠረት፡ በጠቅላላ፡ ምስጢረ-ጥምቀትና ሥርዓቱ፡ የተፈጸመውና የተሠራው፣ የቀረበውም፣ ምንም እንኳ፡ ከእነርሱ መካከል፡ ኹሉም ሊባል ይቻላል፡ በመጨረሻ ሳይቀበሉት የቀሩ ቢኾኑም፡ ከላይ እንደተወሳው፡ ለእነዚሁ፡ ለኹለቱም ወገኖች [ለአይሁድና ለአሕዛብ] ብቻ እንጂ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች አለመኾኑ፡ ተረጋግጦ ሊታወቅ ይገባል።

የዚህ እውነታ፡ ግዙፍ ምስክሩማ፡ በሚከተለው ተጨማሪ ሓተታ፡ ጎልቶ ቀርቧል፡- ይኸውም፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የመምህራችን ቃል እንዳለ ኾኖ፡ ምስጢረ-ጥምቀትና ሥርዓቱ፡ የተፈጸመውና የተሠራው፣ የቀረበውም፣ ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ለኾኑት፡ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት አለመኾኑን፡ በሚበቃ የሚያስረዳው ነው።

አዎን! ገና፡ ጥንት፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡-

-በአዳምና በሔዋን ጋብቻ አማካይነት፡ የህልውና ኪዳንን፣

-በኖኅና በሓይከል ቀስተ-ደመና አማካይነት፡ የአምልኮ ኪዳንን፣

-በመልከ-ጼዴቅና በሳሌም ቍርባን አማካይነት፡ የልጅነት፥ የክህነትና የነጋሢነት ኪዳንን፡ <u>በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔር፡ በባለቤትነት</u> እንደተቀበሉ ኹሉ፣

በመካከለኛውና በመጨረሻው፡ የአረማውያንና የጣዖት አምላኪዎች አሕዛብ ዘመንም፡ የአይሁድ ድርሻ የኾኑትን፡-

-በአብርሃምና በሣራ ግርዛት አማካይነት፡ የተነሳሕያኑን፡ የሃይማኖትና የምግባር ኪዳንን፥

-ደግሞም፡ በሙሴና በሲጳራ አማካይነት፡ የድንግል ማርያምና የኢየሱስ መሲሕ ቀዳሚት አርአያ የኾነችውን፡ የታቦተ-ጽዮንን ጽላተ-ኪዳን፣

-እንዲሁም፡ በዳዊትና በቤትሳባ፣ በማክዳና በሰሎሞን አማካይነት፡ ለዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ የኾነውን ዘውዳዊ የዙፋን ኪዳንን፡ <u>በተዘዋዋሪ፡ ከእግዚአብሔር፡ በአደራነት</u> ተረከቡ።

ስለዚህ፡ ይህን ምስጢረ ጥምቀት፥ ሥርዓቱንም፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ <u>በተዘዋዋሪ፡ ከእግዚአብሔር፡ በአደራ መልክ</u> ተረክበውት፡ እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ፈጸሙት፣ እየፈጸሙትም፡ እስከዛሬ ቀጠሉበት እንጂ፡ በቅዱሱ ኪዳን መለኮታዊና ተፈጥሮአዊ ጸጋ፣ በኪዳነ መልከ-ጼዴቅም ምክንያት፣

-የቅዱሳት ኪዳናቱ ኹሉ፤ መደምደሚያና ማጠቃለያ፥ ቍልፍና ማኅተም ይኾን ዘንድ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ለተገኘው፡ ለመለኮታዊውና ለትስብእታዊው **ኪዳነ ምሕረት፡** ምልክት በኾነው፡ በቅዱሱ ሥጋቸውና በክቡሩ ደማቸው ከጸደቀውና ከጸናው፡ ከመንፈስ ቅዱሳዊውና እሳታዊው የማሕፀን ጥምቀታቸው የተነሣ፡ ለእግዚአብሔር ልጅነት፣ ነጋሢነትና ካህንነት ለበቁት፡ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ አዎን፡ ይህ፡ ምስጢረ ጥምቀት፥ ሥርዓቱም፡ አላስፈለጋቸውም፤ አያስፈልጋቸውምም።

ይህም ኹሉ አማናዊ ኹነታ፡ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ህንደኬ ጃንደረባ በኾነው፡ በዚያ፡ በአዲስ ኪዳኑ ኢትዮጵያዊ አቤሜሌክ ሃይማኖታዊ ምግባር ተከሥቶ ታይቷል። (የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፴፱።)

## እውነተኞቹ የእስራኤል ልጆች፡ የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው።

እግዚአብሔር፡ በዚህ ረገድ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ሳይኾን፡ ለአይሁድና ለአሕዛብም፡ "ይህ ቀረው!" የማይባል፡ ፍጹም ቸርነቱን ያደረገ መኾኑን፡ እዚህ ላይ፡ ባጭሩም ቢኾን፡ ማውሳቱ፡ አግባብ ይኾናል።

ሓዋርያው፡- **"ወርእዩ፡ ዘከመ እፎ ፍቅሩ፡ ዘወሀበነ አብ፡ ከመ ውሉደ እግዚአብሔር ንኩን! ወኮነ።**

"የእግዚአብሔር ልጆች እንድንኾን፡ አብ፡ እንዴት ያለውን ፍቅሩን እንደሰጠን እዩ! ልጆቹም ኾንን።" ያለውን በማዘከር፡ የጥምቀትን በዓል፡ እኛ፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ-ቅዱስ ተወልደንና ለዘለዓለም ሕይወት ተጠርተን፡ "'የእግዚአብሔር ልጆች' የተባልንበትና የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች፥ አገልጋዮቹ ካህናትም የኾንንበት፡ የየራሳችን የልደት በዓል ነው!" ብለን፡ አምነን፡ በንጹሕ ምስጋናና በፍጹም ደስታ የምናከብረው፡ ታላቅ በዓላችን ነው። (፩ኛ ዮሓ. ፫፥ ፩።)

እዚህ ላይ፡ አንድ፡ ሊታወቅ የሚገባው የእግዚአብሔር እውነታ አለ፤ ይኸውም፡ **እውነተኞቹ "የእስራኤል ልጆች"፡ እኛ፡ የቀድሞዎቹ፥ የዛሬዎቹም የኢትዮጵያ ልጆች መኾናችንን፡** በትክክል የመገንዘቡ ቍም-ነገር ነው። የዚህም፡ ምክንያት፡ እንዲህ ነው፡-

፩ኛ፡ እየራሳቸውን፡ "እኛ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የአብርሃምም ልጆች ነን!" እያሉ፡ የሚመጻደቁት "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "የእስራኤል ልጆች"፥ ወይም፡ "አይሁድ" የተባሉት፡ የብሉይ ዘመኑ ኦሪታውያን ወገኖች፡ በአብርሃም ግርዛት፥ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዘር አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተሰጧቸውን፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ አምነውና አጽንተው፥ አክብረውና ጠብቀው መፈጸም ስላቃታቸው፡ እኒሁ፡ ሦስቱም ቃል-ኪዳናት፡ የአብርሃሙ፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ በኬጡራ፥ የሙሴ፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ በሲጳራ፥ የዳዊት፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ በቤትሳባ፥ ከዚያም፡ በልጁ፡ በሰሎሞን አማካይነት፡ በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት፡ በማክዳና በድንግልና ልጇ፡ በምኒልክ በኩል፡ ወደኢትዮጵያ ልጆች፡ በአደራነት ተመልሰው፡ እነሆ፡ በእነርሱ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ለዝንተ-ዓለም፥ እስከዛሬና ለዘለዓለም፡ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን አግኝተው የኖሩ፥ እየኖሩም ያሉ በመኾናቸው ነው።

እንዲሁም፡ ከእነዚያ፡ ከቀደሙት፡ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "የእስራኤል ልጆች"፥ ወይም፡ "አይሁድ" ከተባሉት፡ የብሉይ ዘመኑ ኦሪታውያን ወገኖች መካከል፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በየዘመናቱና በየምክንያቱ፡ ከእነዚሁ ቃል-ኪዳናት ጋር፡ ዐብረው የመጡት፡ የተመረጡትና የበቁት ወገኖች፥ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፡ ከነሥርዓቱ የተቀበሉት፥ እንዲሁም፡ በቅዱሱ ኪዳን ጋብቻ በተገኘው የሥጋ ልደት፡ ከቀደሙት የኢትዮጵያ ልጆች ጋር የተዋሐዱት፡ "እውነተኞቹ የእስራኤል ልጆች" በመኖራቸው ጭምር ነው።

፪ኛ፡ ነገር ግን፡ እየራሳቸውን፡ "እኛ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የአብርሃምም ልጆች ነን!" እያሉ፡ የሚመጻደቁት፥ ደግሞም፡ በአብርሃም ግርዛት፥ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዘር አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተሰጧቸውን፡ ሦስት ቃል-ኪዳናት፡ አምነውና አጽንተው፥ አክብረውና ጠብቀው መፈጸም ያቃታቸው፡ እነዚያ፡ የጥንቶቹ ኾኑ፡ የዛሬዎቹ፡ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "የእስራኤል ልጆች"፥ ወይም፡ "አይሁድ" የተባሉት ኦሪታውያን ወገኖች፡ ቀድሞም፡ በሙሴ ጊዜ፥ በመጨረሻም፡ በኢየሱስ መሲሕ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች፥ ከሃዲዎችና ገዳዮች ኾነው በመገኘታቸው፡ "እስራኤል"፥ ወይም፡ "የእስራኤል ልጆች" ሊባሉ የማይቻል መኾኑን በማረጋገጥ፡ በመለኮታዊው ቃል፡ ምን እንደተባሉ ታውቁ የለምን?

በዚህ ረገድ የተመዘገበውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የአዲስ ኪዳን መጽሓፋዊ ጥቅስ ተመልከቱት፡-

ኢየሱስ መሲሕ፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች፥ ከሃዲዎችና ገዳዮች ኾነው ለተገኙት፡ ለእነዚያ ለቀድሞዎቹና ለእነዚህ፡ ለዛሬዎቹ "ዕብራውያን"፥ ወይም፡ "የእስራኤል ልጆች"፥ ወይም፡ "አይሁድ" ለተባሉት፡ የኦሪታውያን ተከራካሪዎቹ ወገኖች፡ የተናገረው ቃል፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

"'ወአንሰ፡ ዘርኢኩ በኀበ አቡየ፡ እነግር። ወአንትሙሂ፡ ዘርኢክሙ በኀበ አቡክሙ፡ ትገብሩ።'

"ወአውሥኡ፥ ወይቤልዎ፡- 'ለነሰ፡ አብርሃም አቡነ።'

"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሶበሰ ውሉደ-አብርሃም አንትሙ፡ ግብረ አብርሃም፡ እምገበርክሙ። ወይእዜሰ፡ ተኀሥሡ ትቅትሉኒ፥ ብእሴ ጻድቀ፤ ዘጽድቀ እነግረክሙ፤ ዘሰማዕኩ በኀበ እግዚአብሔር፤ ወአብርሃምሰ፡ ኢገብረ ከመዝ። አንትሙሰ፡ ትገብሩ፡ ግብረ አቡክሙ።'

"ወይቤልዎ፡- 'ንሕነሰ፡ ኢተወለድነ እምዝሙት፤ አላ አሐዱ አብ ብነ፤ ወውእቱ እግዚአብሔር።'

"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሶበሰ እግዚአብሔር አቡክሙ፡ እምአፍቀርክሙኒ ኪያየ፤ ወቃልየኒ፡ እምዐቀብክሙ፤ እስመ አነ፡ እምኀበ እግዚአብሔር ወጻእኩ፤ ወመጻእኩ፤ ወአኮ ለልየ ዘመጻእኩ፤ አላ ውእቱ ፈነወኒ። እፎ እንከ፡ ኢተአምኑ ቃልየ? እስመ ኢትክሉ ሰሚዐ፡ ነገረ ዚአየ።

"'<u>አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ፤ ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግበሩ።</u> ወውእቱሰ ቀታሌ ነፍስ ሰብእ ውእቱ እምትካት፤ ወኢይቀውም በጽድቅ፤ እስመ አልቦ ጽድቅ በኀቤሁ፤ ወሶበሂ ይነብብ ሓሰተ፡ እምዚአሁ ይነብብ፤ እስመ ሓሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሃ ለሓሰት።

"'ወአንሰ፡ እስመ ጽድቀ እነግር፡ ወኢተአምኑኒ። መኑ እምኔክሙ፡ ዘይዛለፈኒ፡ በእንተ ኃጢአት? ወእመሰ፡ አነ ጽድቀ እነግር፡ ለምንት ኢተአምኑኒ? <u>ዘሰ፡ እምእግዚአብሔር ውእቱ፡ ቃለ እግዚአብሔር ይሰምዕ፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ አንትሙሰ፡ ኢትሰምዑኒ፤ እስመ ኢኮንክሙ እምእግዚአብሔር።"</u>

"'እኔ፡ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ። እናንተም ደግሞ፡ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።'

"መልሰውም፡- 'አባታችንስ፡ አብርሃም ነው፤' አሉት።

"ጌታችን ኢየሱስም፡- 'የአብርሃም ልጆች ብትኾኑማ፡ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር። አኹን ግን፥ ከእግዚአብሔርም ዘንድ የሰማሁትን እውነት የምነግራችሁን፡ የእውነት ሰው፡ እኔን፡ ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። አብርሃም፡ እንዲህ አላደረገም። እናንተ ግን፡ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ፤' አላቸው።

"እነርሱም፡- 'እኛስ፡ ከዝሙት አልተወለድንም፤ ነገር ግን፡ አንድ አባት አለን፤ እርሱም፡ እግዚአብሔር ነው፤' አሉት።

"ጌታችን ኢየሱስም አላቸው፡- "እግዚአብሔር፡ አባታችሁ ቢኾንማ ኖሮ፡ እኔን፡ በወደዳችሁኝ፥ ቃሌንም፡ በጠበቃችሁ ነበር፤ እኔ፡ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ፡ ላከኝ እንጂ፡ ከራሴ የመጣሁ አይደለሁም። እንኪያ፡ ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ? የምነግራችሁን፡ መስማት አትችሉምና።

"<u>እናንተማ፡ ከአባታችሁ፡ ከሰይጣን ናችሁ፤ የአባታችሁን ፈቃድ ልትፈጽሙ ትወድዳላችሁ።</u> እርሱም፡ ከጥንት፡ የሰው ነፍስ፡ ገዳይ ነው፤ እውነት በእርሱ ዘንድ ስለሌለች፡ ለእውነት አይቆምም። ሓሰትን ሲናገር፡ ከራሱ ይናገራልና፤ ሓሰተኛ፥ የሓሰት አባትም ነውና።

"እኔንማ፡ እውነትን ስለምናገር፡ አታምኑኝም። ከእናንተ፡ ስለኃጢአት የሚወቅሰኝ፡ ማነው? እኔ ግን፡ እውነትን የምናገር ከኾንሁ፡ ለምን አታምኑኝም? ከእግዚአብሔር የኾነ፡ እርሱ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ ስለዚህም፡ እናንተ አትሰሙኝም፤ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና።'" (ዮሓ. ፰፥ ፴፰-፵፯።)

አዎን! በዚህ መሠረታዊ ምክንያት ነው፡ **"እውነተኞቹ እስራኤል፥ የእስራኤልም ልጆች፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የኾኑት፡ የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው እንጂ፡ ዛሬ፡ ራሳቸውን፡ 'እስራኤል ነን!' የሚሉት፤ አይሁድ አይደሉም።**

**ወይም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ራሳቸውን፡ 'ክርስቲያን ነን!' የሚሉትና የቀሩት የዓለም ሕዝብ ወገኖች፡ 'አዎን! «እስራኤል፡ እነዚህ ናቸው!» የሚኗቸው፡ እነዚሁ አይሁድ አይደሉም፡ እስራኤል።"** ያሰኘውና የሚያሰኘው።

## የጥምቀትን በዓል፥
## እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ፥ እንዴት እንደምናከብር?

በዓለ ጥምቀትን፥ እኛ፥ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ፥ ከሌላው፥ የክርስቲያኑ ዓለም ሳይቀር፥ ተለይተን፥ እጅግ በተመሠጠ መንፈሳዊ ስሜት፥ የምናከብርበትን ምክንያት የሚያመለክተውን እውነታ፥ እንዲህ በሚለው፥ አጭር ትንተና በማጠቃለል አቅርበንላችኋልና፥ ይህን ደግሞ፥ ተመልከቱት።

ይኸውም፡-

***፩ኛ፥ "ለእለ ክሕድዎ ቀዲሙ፣ ወነበሩ በንስሓሆሙ፥ እንዘ ይጸንሑ ትዕግሥቶ ለእግዚአብሔር፥ ከመ እለ በመዋዕሊሁ ለኖኅ፥ አመ ይገብር ታቦተ፤ ወድኅኑ ባቲ፣ ሰማኒቱ ነፍስ ኅዳጣን፥ እምነ ማየ አይኅ። ወኪያነኒ፥ ይእዜ ያድኅነነ፥ በአርአያሁ በጥምቀት፤ አኮ፥ በሕፅበተ-ሥጋ፥ እምርስሐት፤ አላ፥ ከመ ግዕዘ ሠናየ፥ ይምህረነ፣ በዘነአምን፥ በእግዚአብሔር፤ ወበተንሥኦቱ፥ ለእግዚእነ ኢየሱስ መሲሕ።***

*"ቀድሞ፥ የክሕደት ኃጢአታቸው፥ በንስሓቸው ይወገድላቸው ዘንድ፥ የእግዚአብሔርን ትዕግሥት፥ ደጅ እየጠኑ ይጠባበቁ ለነበሩት፣ ኖኅ፥ ከጥፋት ውኃ የዳኑባትን መርከብ በሠራበት ዘመን፥ ጥቂቶች ለኾኑት፥ ለስምንቶቹ ሰዎች፥ እንደኾነላቸው ኹሉ፥ አኹንም፥ እኛን፥ በዚያው አምሳል፥ በጥምቀት ያድነናል። ይኸውም፥ የሥጋ ዕድፋችንን፥ በመታጠብ አይደለም፤ ነገር ግን፥ በእግዚአብሔር በማመናችን፣ እርሱም፥ በበጎ ኅሊና በሚያስተምረንና በጌታችን ኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ ነው እንጂ።" በሚለው፥ የመጽሐፍ ቃል መሠረት፥ እግዚአብሔር፥ የኪዳነ-ልቦናዋን የኖኅ መርከብ፥ በኢትዮጵያ ባሕረ-ነጋሽ (በኤርትራ) ላይ ያሻገረበት፥ መለኮታዊና ምስጢራው ሥርዓቱ፥ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፥ ከጥንት ጀምሮ፥ ተጠብቆ፥ ሲሠራበት የቆየ በመኾኑ ነው፤ (፩ጴጥ. ፫፥ ፳-፳፩።)*

*፪ኛ፥ ሙሴን የተካው ኢያሱ፥ የኪዳነ-ኦሪቷን፥ የእግዚአብሔር ታቦት፥ በተሸከሙ ካህናት፥ የእስራኤልን ሕዝብ፥ በዮርዳኖስ ባሕር የማሻገሩ ዜና መዋዕል፥ ዐብሮ የሚገኝበትን፣ ቀደም ብለን ያወሳንላችሁን፥ የታቦተ-ጽዮንን ዝክረ-ነገር የሚያካትተው፥ የኪዳነ-ኦሪቱ ሥርዓት፥ በኢትዮጵያ፥ ከቀደመው ጋር ተዋሕዶ፥ እንዲቀጥል በመደረጉ ነው፤ (ኢያ. ፫፥ ፩-፲፯።)*

፫ኛ፡ ትንቢቱ ኹሉ ተፈጽሞ፥ ተስፋውም ኹሉ ደርሶ፡ እግዚአብሔር፡ ሰው መኾኑ ከተገለጸ በኋላ፡ በመጥምቁ ዮሓንስ ይካኼድ የነበረው፡ የንስሓ ጥምቀት ሳይቀር፡ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ለኒቆዲሞስ ባስተማረው የጥምቀት ምስጢር መሠረት፡ የኪዳነ-ልቦናውና የኪዳነ-ኦሪቱ ሥርዓታት፡ ኹሉም፡ በአዲሱ ኪዳነ-መንፈስ ቅዱስ ታድሰው፡ ዛሬ፡ በኢየሱስ መሲሕ ምሳሌ፡ የአዲስ ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት፡ ወደወንዙ፥ ወይም፡ ወደከተራው ውኃ የሚወርዱበት ሥርዓት በመተካቱ ነው። (ዮሓ. ፫፥ ፩-፲፮።)

እኛ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚህ በዓላችን ጊዜ፡

**"ሃሌ፣ ሃሌ፣ ሃሌ፣ ሃሌ ሉያ!**
**"ተጠምቀ ሰማያዊ፣ በእደ መሬታዊ!"**

"ከዓለም-ፍጥረት በፊት፣ አስቀድሞ የነበረው፣ ዛሬም ያለውና ፍጥረተ-ዓለሙንም አሳልፎ፡ ለዘለዓለም የሚኖረው፡ እርሱ፡ የኹሉ ፈጣሪና የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር፤ የማይታይና የማይዳሰስ፣ ሰማያዊና መለኮታዊ ረቂቅ ሲኾን፣ በሚታየውና በሚዳሰሰው፥ በግዙፉ ሰብኣዊና ምድራዊ እጅ ተጠመቀ!"

ደግሞም፡ **"ጎዲጎ ተስዓ፣ ወተስዓተ ነገደ!**
**"ማእከለ ባሕር፣ ቆመ ማእከለ ባሕር!"**

"ዘጠና ዘጠኙን (ነገደ-መላእክት)፡ በሰማያት ትቶ፣
"የጠፋውን አንዱን (የአዳምንና የሔዋንን ነገድ) ሊፈልገው መጥቶ፣
"ማግኘቱን ለፍጥረት፡ ባዋጅ አሳወቀ፤
"በባሕር መካከል ቆሞ፡ ተጠመቀ።"

እንዲሁም፡ **"መሲሕ፡ ተጠምቀ እሰይ!**
**"ወለደነ፡ ዳግመ እማይ!**

"መሲሕ ኢየሱስ ስለተጠመቀ፡ ደስ ይበለን!
እኛም፡ በጥምቀት፡ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ፡ እንደገና እንድንወለድ አደረገ!" ከሚለው ዝማሬያችን ጋር፡
**"ዮም ፍሥሓ ኮነ! በእንተ ጥምቀቱ ለኢየሱስ መሲሕ!"**
"ዛሬ፡ ታላቅ ደስታ ኾነ!
"እግዚአብሔራችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ተጠምቋልና!"

የሚለውን የምሥራች ቃል እንለዋወጣለን።

ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ እንደዘመነ ትንሣኤ፡ እስከ ጥር ፴ ቀን ድረስ ይቀጥላል።

## የጥምቀት በዓላችን፡ ጥር ፩ ቀን ስለመኾኑ።

እኛ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ **በዓለ አስተርእዮቱንና ጥምቀቱን**፡ በመታሰቢያነት፡ በየዓመቱ፡ ልናከብረው የሚገባን፡ እስካኹን ሲፈጸም በኖረው፤ አኹንም፡ እየተፈጸመ ባለው፡ በባዕዳኑ ጥር ፲፩ ቀን ሳይኾን፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ከመጀመሪያው አንሥተው፡ ይፈጽሙትና ያከብሩበት ወደነበረው ወደጥንታዊው ጥንተ ዕለቱ፡ በይፋ ተመልሶ፡ በ**ጥር ፩ ቀን** እንዲኾን፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ፡ በመለኮታዊው ዐዋጅ፡ ራሷን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ የገለጠችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በቁጥር ፲፫/፳፻፰ ዓ. ም. በአሰማችው፡ የዐዋጅ ቃሏ፡ አምላካዊ መመሪያን በመስጠቷ ነው።

ይህ አምላካዊ መመሪያ፡ በመለኮታዊው ዐዋጅ እንዲሰጥ አስፈላጊ የኾነውም፡ ያለምክንያት አይደለም። ለዚችው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የታወቁት ተፃራሪዎቿ የኾኑት፡ በይበልጥ፡ የኦሪታውያኑ አይሁድ ካህናትና የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መነኮሳት፡ ከሌሎቹ መሰሎቻቸው ወገኖች ጋር ተመሣጥረውና ተባብረው፡ በእርሷ ላይ ሲያካኼዱ የኖሩትን የጥፋት ዘመቻቸውን፡ ፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ ያውቀዋል። በመስከረም ፩ ቀን ይውል የነበረውን፥ የኢትዮጵያ ልጆችም፡ በዚያው ዕለት ያከብሩት የነበረውን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን እና የልጇ የወዳጇ ን፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን የልደታት ቀን፡ ከዚያ ጥንተ ዕለቱ አንሥተው፡ ወደታኅሣሥ ፳፱ ቀን ማምጣታቸው ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬም እንኳ፡ ያው የመስከረም ፩ዱን ቀንም፡ በእነርሱ፡ የዐሥር ቀኖች የጭማሪ ልዩነት እንዲኖረው አድርገው፡ ወደSeptember 11 (ሴፕቴምበር ኢለቨን)ንነት የለወጡት፡ በዚያ ዘመቻቸው እንደነበረ ኹሉ፤

አኹንም፡ ልክ እንደዚያው ሓሳዊ ድርጊታቸው፤ **ጥር ፩ ቀን** ይውል የነበረውን፥ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆችም፡ በዚያው ዕለት ያከብሩት የነበረውን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ የጥምቀት ቀን፡ ይህንኑ ዐሥር ቀናቸውን በመጨመር፡ በተለመደው ድፍረታቸውና ማናለብኝነታቸው፡ ወደጥር ፲፩ ቀንነት እንዲለወጥ አድርገውት ስለነበረ ነው።

የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የትስብእታዊ ፅንሰቱ ዕለት፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን፥ የትስብእታዊ ልደቱ ዕለት፡ መስከረም ፩ ቀን፥ የትስብእታዊ ትንሣኤው ዕለት፡ ሚያዝያ ፩ ቀን እንደመኾኑ መጠን፤ የትስብእታዊ ጥምቀቱም ዕለት፡ በጥር ፩ ቀን መኾኑ፡ እያንዳንዱ መለኮታዊ ትንግርት የተፈጸመው፡ አንድ ዓይነት በኾነው፡ በየወራቱ መባቻ [መግቢያ] ላይ መኾኑን ያረጋግጣል።

## የጥር ሥላሴ።

ከበዓለ-ጥምቀት፡ ጥቂት ዕለታት በኋላ ተከትሎ፡ በጥር ፯ ቀን፡ "የጥር ሥላሴ" በዓል ይከበራል። ይህም የኾነው፡ ቀደም ብሎ፡ በታኅሣሥ ፩ እና ፯ ቀናት በሚውሉት፡ በሰላማችን፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እና እግዝእተብሔር እም፡ ቀደም ብላ በተዋሓደቻት፡ በመድኃኒታችን፡ በቅድስት እናቱ ትስብእት፣ አምላክ ሰው ኾኖ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን በመፀነሱ፡ የእግዚአብሔር፡ የአንድነቱና የሦስትነቱ ምስጢር ስለተከሠተ፣ ስለታወቀና ስለተረዳ፡ የምስጢረ-ሥላሴና የምስጢረ-ሥጋዌ ነገር፡ በሰፊው እየተነገረ፡ ትምህርቱ እንዲሰጥበት፥ ምስጢሩም እንዲፍታታበት ታስቦ ነው።

ይኸው የቅድስት ሥላሴ ዓመታዊ በዓል፡ ጥር ፩ ቀን ከሚከበረው፡ ከጥምቀት በዓል በኋላ መዋሉ፡ በትክክለኛነቱና በአግባብነቱ ረገድ፡ እውነታው፡ እንዴት ሊሠምር እንደቻለ መገመቱ፡ ለማንም አስተዋይ ተመልካች አያዳግትም።

በዚህ ጊዜ፡ "አስተርእዮ"፡ ማለትም፡ "የእግዚአብሔር ሰው ኾኖ የመገለጡ ምስጢር"፡ በግልጽና በገሃድ፥ በይፋና በዐዋጅ በሚነገርበት ወራት ውስጥ መግባታችንን እናረጋግጣለን። ከበዓለ-ጥምቀት ዕለት ጀምሮ፡ በዚሁ ወራት፡ የሚነገረውና የሚሰማው፥ የሚሰበከውና የሚዘመረው፡ ስለምስጢረ ጥምቀት፥ ስለምስጢረ-ሥላሴና ስለምስጢረ-ሥጋዌ ይኾናል።

## ቃና ዘገሊላ።

ኢየሱስ መሲሕ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ፡ በዐዋጅ ነጋሪው ዮሐንስ እጅ፡ በተጠመቀ ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ሰው የኾነው፡ የእርሱ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ማንነት፡ በይፋ ተገልጦ ከታወቀ ወዲህ፡ ብዙም ሳይቆይ፡ ተከታትሎ፡ ይኸው የቅድስት እናቱ እና የእርሱ መለኮታዊ ማንነት፡ በበለጠ ግዙፍ ማስረጃ የተረጋገጠበት፡ የመጀመሪያው ተአምር፡ "ቃና ዘገሊላ" በምትባለው ቦታ፡ ተፈጽሞ ታየ። ከጥምቀትና ከቅድስት ሥላሴ በዓላት ቀጥሎ የሚከበረው፡ "የአስተርእዮ" በዓል፡ "ቃና ዘገሊላ" ይባላል።

"ገሊላ"፡ ዋና ከተማው፡ "ናዝሬት" የኾነ፡ ቀድሞ፡ የፍልስጥኤም፥ በአኹኑ ጊዜ፡ የእስራኤል ክፍለ-ሀገር፥ ወይም፡ አውራጃ ሲኾን፡ "ቃና"፡ በገሊላ የምትገኝ፡ መንደር ናት። በዓሉ፡ "ቃና ዘገሊላ" የተባለበትም ምክንያት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለግብዣ ተጠርተው፡ በተገኙበት ሠርግ ላይ፡ እርሷ፡ በእናትነት፥ ልጇም፡ በልጅነት ደረጃ ተነጋግረው፡ የመጀመሪያው ታላቅ ተአምር፡ የተፈጸመበትና የታየበት ቦታ፡ "ቃና ዘገሊላ"፥ ወይም፡ "የገሊላዋ ቃና" እየተባለ፡ የሚጠራ ስለኾነ ነው።

## ድንግል ማርያም፡
## እግዚአብሔር እም መኾኗና አምላካዊ ቸርነቷ፡
## በይፋ የተገለጸበት ሠርግ።

የቃና ዘገሊላ ዝክረ-ነገር፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ይህን ያህል፡ ከፍተኛ ግምትና ልዩ ድምቀት ተሰጥቶት፡ በዚህ መልክ የሚከበረው፡ ያለምክንያት አይደለምና፡ ይህንኑ ምክንያት እንግለጽላችሁ!

በዚያ ሠርግ ላይ የኾነውንና የደረሰውን ኹሉ፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ እንዲህ ሲል ጽፎታል፡- "**ከብካብ ኮነ፣ በቃና ዘገሊላ። ወሀለወት ህየ፡ እሙ፡ ለእግዚእ ኢየሱስ። ወጸውዕዎ ለእግዚእ ኢየሱስ፥ ወለአርዳኢሁ፡ ውስተ ከብካብ።**

**"ወሶበ ኀልቀ ወይኖሙ፡ ትቤሎ እሙ ለእግዚእ ኢየሱስ፡- 'ወይንኬ አልቦሙ።'**

**"ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ምንት ብየ ምስሌኪ፣ አ ብእሲቶ! ዓዲ፡ ኢበጽሐ ጊዜየ።'**

**"ወትቤሎሙ እሙ፡ ለእለ ይትለአኩ፡- 'ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!'**

**"ወሀለዋ ህየ መሣክብት ስድስቱ፡ እለ እብን፡ በዘያጥህሩ ቦቶን አይሁድ፡ ንቡራት ህየ፤ ወያገምራ፡ በበክሌቱ፥ ወበበሠለስቱ መስፈርት፡ ዘቀሡት።**

**"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ምልእዎንኬ፡ ለእላ መሣክብት፡ ማየ፣ እስከላዕሎን፤ ወእስከአፉሆን!'**

**"ወይቤሎሙ፡- 'ቅድሑኬ ይእዜ፤ ወሰዱ! ወሀብዎ፣ ለሊቀ ምርፋቅ!'**

**"ወወሰዱ፤ ወወሀብዎ።**

**"ወጥዒሞ፡ አንከረ ሊቀ-ምርፋቅ፣ ውእተ ማየ፡ ዘኮነ ወይነ፤ ወኢያእመረ፡ እምኀበ አምጽእዎ፤ ወገዛእትሰ፡ እለ ቀድሕዎ፡ የአምሩ፡ ውእተ ማየ፣ ዘኮነ ወይነ፤ እስመ እሙንቱ፡ መልኡ ማየ። ወጸውዖ ሊቀ-ምርፋቅ፡ ለመርዓዊ፤ ወይቤሎ፡- 'ኵሉ ሰብእ፡ ዘይሤኒ ወይነ፡ ያቀድም አስትዮ፤ ወእምድኅረ ሰክሩ፡ ያሰቲ፡ ዘይቴሐት፤ ወአንተሰ፡ ዘይሤኒ ወይነ፡ ዐቀብከ፤ ወአስተደንገርከ እስከ ይእዜ።**

**"ወዝንቱ፡ ቀዳሚ ተአምር፡ ዘገብረ፡ እግዚእ ኢየሱስ፡ በቃና ዘገሊላ፤ ወአርአየ ስብሐቲሁ፤ ወአምኑ ቦቱ፡ አርዳኢሁ።**

"በገሊላ ቃና፡ ሠርግ ነበረ፤ የጌታችን የኢየሱስም እናት፡ በዚያ ነበረች፤ ጌታችን ኢየሱስ፣ ደቀ-መዛሙርቱም ደግሞ፡ ወደሠርጉ ታደሙ።

"የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ፡ የጌታችን ኢየሱስ እናት፡- 'የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም!' አለችው።

"ጌታችን ኢየሱስም፡- 'እናቴ ሆይ! ለምን ታስቸግሪኛለሽ? ጊዜዬ እኮ ገና አልደረሰም!' አላት።

"እናቱም፡ ለቋሚዎቹ አገልጋዮች፡- 'ልጄ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!' አለቻቸው።

"አይሁድ፡ ስለማንጻት ልማዳቸው ለሚያደርጉት ወግ፡ የሚጠቀሙባቸው፡ ስድስት የድንጋይ ጋኖች፡ በዚያ ተቀምጠው ነበር፤ እያንዳንዳቸውም፡ ኹለት፥ ወይም፡ ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር።

"ጌታችን ኢየሱስም፡- 'ጋኖቹን፡ እስከላይ፣ እስከአፋቸው ድረስ፡ ውኃ ሙሏቸው!' አላቸው።

"ከሞሏቸው በኋላም፡ 'አኹን ደግሞ፡ ቀድታችሁ፡ ውሰዱና፡ ለአሳዳሪው ስጡት!' አላቸው። ወስደውም ሰጡት።

"አሳዳሪውም፡ የወይን ጠጅ የኾነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ፡ አደነቀ፤ ከወዴት እንዳመጡትም፡ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አሳላፊዎች ግን፡ ወይን ጠጅ ስለኾነው፡ ስለዚህ ውኃ፡ በትክክል ያውቁ ነበር፤ ጋኖቹን፡ በውኃ የሞሉት፡ እነርሱ ነበሩና። አሳዳሪውም፡ ሙሽራውን ጠርቶ፡ እንዲህ አለው፡- 'ሰው ኹሉ፡ አስቀድሞ፡ ማለፊያውን የወይን ጠጅ፥ ከሰከሩም በኋላ፡ መናኛውን አቅርቦ ያጠጣል፤ አንተ ግን፡ ማለፊያውን የወይን ጠጅ፡ እስካኹን፡ ወደመጨረሻ አቆየህ!'

"ጌታችን ኢየሱስ፡ የገሊላ አውራጃ በምትኾን፡ በቃና ያደረጋት፡ የተአምራቱ መጀመሪያ፡ ይህች ናት፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ-መዛሙርቱም፡ በእርሱ አመኑ።" (ዮሐ. ፪፥ ፩-፲፩።)

*ይህ፡ የወንጌላዊው ቃል፡ የሰው ልጆች ለኾንነው ኹሉ፣ በተለይም፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ በቍም-ነገር ልናስተውላቸው የሚገቡ መልእክቶችን አስተላልፎልን እናገኘዋለን። እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-*

*፩ኛ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም እና የልጇ የወዳጇ የኢየሱስ መሲሕ፡ በዚያ የሠርግ በዓል ላይ መገኘት፡* "**ወይከውኑ ክልኤሆሙ፡ አሓደ ሥጋ። እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ፡ አሓዱ ሥጋ እሙንቱ። ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ!**

*"ባልና ሚስት፡ ኹለቱም፡ አንድ ሥጋ ይኾናሉ፤ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፣ ወደፊት ኹለት አይደሉም፤ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አንድ ያደረገውን፡ እንግዴህ፡ ሰው፡ አይለየው!" ብሎ፡ ፈጣሪ አምላክ፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በአዳም እና ሔዋን የመሠረተው፣ የኢትዮጵያ ልጆችም፡ በኪዳነ ልቦናና በኪዳነ አሪት፡ ጠብቀው ያኖሩት፡ የብሉዩ ኪዳን፡ የጋብቻ ሥርዓት፡ አዲሱ የምሕረት ኪዳን በኾነው፡ በኪዳነ-መንፈስ ቅዱስም፡ መጽናቱንና መጽደቁን፣ መብባረኩንና መቅቀደሱንም አረጋግጦልናል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፪፥ ፳-፳፭። ማቴ. ፲፱፥ ፫-፯።)*

*፪ኛ፡ የሠርጉ በዓል፡ በእርግጥ፡ የኢየሱስ መሲሕ ማንነትና ክብር፡ በይፋ የተገለጠበት መኾኑን፡ ራሱ፡ የወንጌላዊው ቃል፡ በሚበቃ ያስረዳል።*

*በዚያ ቃል መሠረት፡ ያ፡ "ይወርዳል! ይወለዳል!" ተብሎ፡ ትንቢት እየተነገረለትና ሱባኤ እየተቈጠረለት፣ በተስፋ የሚጠበቀው መሲሕ፡ በመኻከላቸው የተቀመጠው፡ የማርያም ልጅ፡ ኢየሱስ መኾኑን፡ የልጇን ማንነትና ክብር፡ ከፅንሰቱ ጀምራ ከምታውቀው፡ ከእናቱ፡ ከድንግል ማርያም በቀር፡ ደቀ-መዛሙርቱና የሠርጉ ደጋሾች፣ እኒህ አሳላፊዎችና ሌሎቹ ዕድምተኞች፡ አረጋግጠው ዐውቀዋል፤ አምነውማል።*

*ይህም የኾነው፡ ንጹሑን ውኃ፡ በፊታቸው፡ ወደወይን ጠጅነት ለውጦ፡ ብርቅ የኾነባቸውን ማለፊያነቱን እያደነቁና እያጣጣሙ እንዲጠጡት ያደረገበትን ተአምሩን፡ በገዛ ዓይናቸው ስለተመለከቱ ነው። ያን፡ ድንቅ ሥራ ያዩት ኹሉ፡ "ሰው የኾነው፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱ ነው!" ብለው ከማመን፣ የአምላክነቱንም ክብር፡ ዐውቀው ከመቀበል በቀር፡ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። ለዚህ እውነታ ምስክርነት፡* "**ጌታችን ኢየሱስ፡ የገሊላ አውራጃ በምትኾን፡ በቃና ያደረጋት፡ የተአምራቱ መጀመሪያ፡ ይህች ናት፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ-መዛሙርቱም፡ በእርሱ አመኑ።**" *የሚለው፡ የወንጌላዊው መዝጊያ ዐረፍተ-ነገር፡ የሚበቃ ይኾናል።*

፫ኛ፡ እግዚአብሔር፡ ያ፡ መለኮታዊ ትንግርት፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ እንዲፈጸም፥ ያም ተአምር ተጽፎ፡ ከትውልድ፡ ወደትውልድ እየተላለፈ፡ የዓለም ሕዝብና አሕዛብ እንዲያነብቡት ያደረገው፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ ማንነትና ክብር፡ እንዲገለጽ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ የእናቱ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ማንነትና ክብር፡ በይፋ እንዲታወቅ ለማድረግ መኾኑ፡ ከራሱ፡ ከወንጌላዊው ቃል፡ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ይኸውም፡ **"እናቴ ሆይ! ለምን ታስቸግሪኛለሽ? አንቺ፡ እግዝእተብሔር እም፡ በተዋሓድሻት፡ እኔም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በተወለድኋት፡ በድንግል ማርያም መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ የፈጠርነውን ዓለም፡ ለማዳንና ሰላሙን ለማቀዳጀት፤ በሰውነት መገለጣችንን፡ ለዓለሙ የምናሳውቅበት ጊዜ እኮ፡ ገና አልደረሰም!"** የሚለው ነው።

ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ማንነቱን፡ በይፋ የገለጸባቸው፡ ሌሎቹ፡ ብዙዎቹ፡ ታላላቅ ተአምራቱ፡ ገና ወደፊት ተከታትለው የሚፈጸሙ ስለኾነ፡ ይህ፡ የቃና ዘገሊላው የሠርግ በዓል፡ ለኢየሱስ መሲሕ ማንነትና ክብር መገለጫ እንዲኾን የማስፈለጉ ነገር፡ ይህን ያህል ክብደት፡ የሚሰጠው መስሎ አለመታየቱን፡ የጥቅሱ ኃይለ-ቃል በግልጽ ያመለክታል። ይልቅስ፡ የቃና ዘገሊላው የሠርግ ዐውድማ፡ በመለኮታዊው ዕቅድ የተዘጋጀው፡ ያለጥርጥር፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ማንነትና ክብር መገለጫ እንዲኾን ታስቦ መኾኑን፡ ከዐውድማው የተሰበሰበው የሃይማኖት ፍሬ፡ በሚበቃ ያረጋግጣል።

፬ኛ፡ “ልጄን፡ በሠርግ እድራለሁ!” የሚል፡ ማንም ጨዋ ቤተሰብ፡ የሚያዘጋጀው የድግሥ መጠን፡ ከሚጋብዛቸው ዕድምተኞች፤ ማለትም፡ ከሚጠራቸው ተጋባዦች በላይ የሚትረፈረፍ መኾኑን፤ ያም ባይኾን፤ የሚበቃ መኾኑን፡ በቅድሚያ ዐውቆና አረጋግጦ የማይዘጋጅ ማነው? ገበታውስ የሚሰናዳው፡ የተጠራው ሰው ብዛት፡ ታውቆ አይደለምን? አዎን ነው። ይህም ኾኖ፡ ከሙሽራው ጋር የሚመጡት ሠርገኞች፡ ቍጥራቸው እንዲታወቅ፡ ይደረግ የለምን? አዎን!

ታዲያ! ይህ ኹሉ ጥንቃቄ፡ አስቀድሞ የሚደረገው፡ የተዘጋጀው ድግሥ አንሶ፡ በቤተሰቡ ላይ፡ ኀፍረትና ውርደት እንዳይደርስ ለማድረግ አይደለምን? አዎን! ነው። ድንግል ማርያም እና ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ ብቻ ሳይኾኑ፡ የልጇ የወዳጇ ደቀ-መዛሙርት ጭምር ተጠርተው ከመጋበዛቸው ጋር፡ ቅድስቲቱ የአምላክ እናት፡ **"የወይን ጠጅ እኮ አልቆባቸዋል!"** ብላ፡ የቤተሰቡን ገመና፡ ለልጇ ለወዳጇ፡ በቀስታ ማዋየቷ፡ ያ ሠርግ፡ የቅርብ ቤተ-ዘመዳቸው በዓል መኾኑን፡ አረጋግጦ ያሳያል።

ታዲያ! ይህን የመሰለው አሳፋሪ ኹኔታ፡ በዚያ የዘመድ ቤተሰብ ላይ እንዲደርስ፡ በግብዣው ላይ የተሳተፈው መንፈሰ-እግዚአብሔር፡ ለምን ፈቀደ? ያ ሠርግ፡ ለመለኮታዊ ዓላማ ማስፈጸሚያ፡ በመለኮታዊ ዕቅድ፡ ኾን ተብሎ የተዘጋጀ መድረክ፥ ወይም ዐውድማ ቢኾን አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፡ በመለኮታዊው ዕቅድ የተዘጋጀው፡ ያ መለኮታዊ ዓላማም፡ <u>**የቅድስት ድንግል ማርያምን ማንነትና ክብር፡ ለሰው ልጆች ኹሉ ለመግለጽና ለማሳወቅ መኾኑ፡**</u> በዚህ ይታወቃል።

፫ኛ፡ በዚያ የሠርግ በዓል ላይ፡ በተፈጸመው ተአምር ምክንያት፡ የኢየሱስ መሲሕ አምላክነት ታውቆ፡ መለኮታዊ ክብሩ፡ በሰዎች ዘንድ እንደተገለጠ ኹሉ፡ እስከዚያች ቀን ድረስ፡ ሰውና የሰው እናት ብቻ ትመስላቸው የነበረችው፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን የወለደች፡ የአምላክ እናት ብቻ ሳትኾን፡ ራሷም፡ እግዝእተብሔር እም እና አምላክ መኾኗ፡ በይፋ ታውቆ፡ ይህ፡ አማናዊ ማንነቷና ክብሩዋ፡ በሰዎችም፥ በፍጥረተ-ዓለሙም ዘንድ፡ በገሃድ ተከሥቶ ተረጋግጧል።

፬ኛ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ራሷ፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት በመኾኗ፤ በመለኮትነቷም፤ በሰውነቷም፡ የአምላክ እናት በኾነችበት፡ በዚህ ማንነቷና ክብሩዋ፡ እንደፈጣሪ አምላክ፡ ኹሉን ለማድረግ የሚሳናት፡ አንዳችም ነገር አለመኖሩ፥ ለበጎ ነገር ከኾነም፡ ፈጣሪ አምላክ፡ ሊያደርግ የማይፈልገውን እንኳ፡ በእናትነቷ፡ ማስደረግ የምትችልበት ሥልጣን ያላት መኾኗ፡ በዚያ ሠርግ ላይ፡ ያለውልውል፡ በይፋ ተመስክሯል።

ይኸውም፡ **"የወይኑ ጠጅ ስላለቀባቸው፡ ሊኾንላቸው የሚገባውን፡ ማድረግ ትችላለህና፡ ልጄ! እኒህን ሰዎች፡ ከዚህ ኀፍረት አውጣቸው!"** በሚል መልክ፡ እርሷ ያቀረበችለት ጥያቄ፡ የምስክሩ መነሻ ነው።

እርሱ ደግሞ፡ በቁርጥ ቃል፡ የሰጣት መልስ፡- **"ምንም እንኳ፡ እግዝእተብሔር እም በመኾንሽ፡ ከፍጥረተ-ዓለሙ በፊት፡ አስቀድመሽ፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በፍጥረተ-ዓለሙ የፍጻሜ ዘመን፡ በሰውነት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከእግዚአብሔር አብ የወለድሽኝ በመኾንሽ፡ በእኔ ዘንድ የማስበውንና የማደርገውን ኹሉ የምታውቂ እናቴ ብትኾኚም፥ በእግዚአብሔር ወልድነቴና ፈጣሪነቴ፡ ይህን ማንነቴን፡ ለፍጡሬ የማሳውቅበትን ተአምር ልፈጽምበት የወሰንሁት ጊዜዬ፡ ገና ስላልደረሰ፡ የጠየቅሽውን ላደርግ አልችልምና፡ እባክሽ ተዪኝ!"** የሚል መልክ እንደነበረው፡ ከቃሉ ለማስተዋል፡ ለማንም አያዳግትም።

ይኹን እንጂ፡ ልጁ ወዳጁ ኢየሱስ መሲሕ፡ ይህን የመሰለውን ምላሽ የሰጣት፡ እናቱ፡ ምን ዓይነቱ፡ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳላት፡ ከዚህ የቀጠለው፡ የእናቱ ድርጊት፡ በገሃድ ያሳያል። ይኸውም፡ ይህችው እናቱ፡ እዚያው፡ በልጁ ዘንድ ቆይታ፡ ሌላ፡ ተጨማሪ ችግሮችን እያከታተለች በማቅረብ፡ ምልጃዋን አጠናክራ ልትቀጥል ሲገባትና ስትችል፡ ያን ማድረጓን ትታ፡ በቀደመው ምልጃዋ፡- **“ልጄ ሆይ! የአንተንም፤ የእኔንም መለኮታዊ ማንነት፡ ለዓለሙ ልትገልጥበት የወሰንኸው ጊዜህ ባይደርስም እንኳ፡ እባክህ! ለእኔ ስትል፡ ፈቃዴን ፈጽምልኝ!”** እንዳለችው በሚያስገነዝብ ኹኔታ፡ ከልጁ ዘወር ብላ፡ በዚያ ፋንታ፡ አሳላፊዎች አገልጋዮቹን ጠርታ፡- "**ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!** ልጄ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!" በማለት የተናገረችው፡ አጭር ቃል ነው።

ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ይህን፡ ራሷ፡ በቀጥታ የሰጠቻቸውን ትእዛዝ፡ ወዲያው የፈጸሙት፡ እነርሱ፡ አገልጋዮቹ ብቻ አይደሉም፤ ፈጣሪ አምላክ የኾነው ልጁም፡ ያለአንዳች ተጨማሪ፥ ወይም፡ ተከታይ ጥያቄ፡ በፍጹም ታዛዥነት፡ በተግባር ላይ ዐውሎ፡ ለፍጻሜ አበቃው እንጂ።

በዚህ፡ በእናቲቱ ትእዛዝ መሠረት፡ አገልጋዮቹ፡ ወደእርሱ፡ ወደልጁ፡ ወደወዳጁ፡ ወደኢየሱስ መሲሕ ቀርበው፡ "**እናትህ፡- 'ልጄ፡ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!' ብላ፡ ወደአንተ ላከችን፤ ምን እንድናደርግ ትወድዳለህ? እዘዘን!**" ብለው፡ በፊቱ በቆሙ ጊዜ፡ ወደእናቱ ኼዶ፡- "**ምነው እናቴ? ያልሁሽን አልተረዳሽልኝም እንዴ? ምነው፡ እንዲህ አጋለጥሽኝ? 'አይኾንም!' ብዬሽ አልነበረምን?**" አላለም። የልቧን አሳብና ፍላጎት ስላወቀው፡ ከእርሷ፡ ተጨማሪ ምላሽን፥ ወይም፡ ማብራሪያን ሳይጠይቅ፥ ሳይጠብቅም፡ የእናቱን ትእዛዝ፡ ያለአንዳች ማመንታት፥ ወይም፡ ማወላወል፡ በቀጥታ ፈጸመ።

፪ኛ፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት፡ እርሷ እናቱ ድንግል ማርያም፡ የሰውን ዘርና ዓለሙን ኹሉ ልታድን፥ እርሱም፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ ሰላምን ሊያስገኝ፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ የግብዣውን ጥሪ ተቀብሎ፣ ራሱም ተገኝቶ፡ እየተጋበዘበት ባለው፡ በዘመዶቹ ሠርግ ላይ፡ ይህን የመሰለ ችግር መድረሱን ሲያውቅ፡ ቀድሞውንስ ቢኾን፡ እንዴት ዝም አለ? ከዚህም በላይ፡ እናቱ፡ ለእርሱ የሚቻለው መኾኑን እያወቀች፡ ለተቸገሩት ዘመዶቻቸው፡ ያን፡ እጅግ አስፈላጊና አስቸኳይ የኾነ እርዳታን እንዲያደርግላቸው ስትጠይቀው፡ ያን የመሰለ፡ ርኅራኄና ኀዘኔታ የጎደለው ያስመሰለውን፡ ከባድ፡ የአሉታ ምላሽስ፡ እንዴት ሊሰጣት፡ ወድዶ መረጠ? ይህ፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ መሲሕ ኹኔታ፡ ለማያምን ብርቱ ቀርቶ፣ ለሚያምን ደካማም ቢኾን፡ ግራ የሚያጋባ ነገር ኾኖ ይታያል።

ነገር ግን፡ ለምን፡ እንዲህ ያለው ነገር እንዲደርስ፡ ፈቃዱ እንደኾነ ለመረዳት፡ ቀደም ብሎ ወደተጠቀሰው፡ ወደመለኮታዊው ዕቅድና ዓላማ፡ መለስ ብሎ ማስተዋልን ይጠይቃል። **ዕቅዱና ዓላማው እኮ፡ የቅድስት እናቱን ማንነትና ክብር፡ ለመግለጥ ስለኾነ፤** መድረኩን፡ ለእርሱ ማንነትና ክብር መገለጫ ሳይኾን፤ በቅድሚያና በይበልጥ፡ ለእርሷ ማንነትና ክብር መገለጫ እንዲኾን መልቀቁን፡ በማስተዋል መመልከት ነው።

**የቅድስት ድንግል ማርያም ክብርዋ፡** እስከዛሬ ታምኖበት እንደተኖረው፡ አማላጅነቷ ብቻ አይደለም፤ **እግዚአብሔር እም እንደመኾኗም፡ በራሷ መለኮታዊ ፈቃድ፡ ኹሉን ማድረግ የማይሳናት መኾኑ ጭምር ነው እንጂ።** ይኸውም፡ "የእናት ምልጃ፡ ፊት አያስመልስ! አንገት አያስቀልስ!' እንደሚባለው፡ ይህን የመሰለው መለኮታዊ ቸርነት፡ ይደረግላቸው ዘንድ፡ ማንነቷንና ክብሯን፡ በአማላጅነት ደረጃ ብቻ እንኳ የወሰኑት ሰዎች፡በፍጹም ሃይማኖት ኾነው፡ በስሟ፡ ወደእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋናና ጸሎት፡ በቋሚ ምልጃዋ፡ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን ማስገኘቱ ነው።

የሰው ልጆች፤ ራሳቸውን፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት ካበቁ፡ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል፡ ጣልቃ ገብተው፡ የመለኮትን ምሕረት ለማስገኘት የሚችሉበትን፡ የአማላጅነት ሥልጣን ሊሰጣቸው፡ እግዚአብሔር፡ ፈቃዱ እንደኾነ፡ በዚህ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም አሳሳቢነት በፈጸመው፡ በአዲሱ ኪዳን መለኮታዊ ተአምራቱ፡ አረጋግጦ አሳይቷል። ያሳየውም፡ ይህ፡ የመለኮት ቸርነት፡ እየራሳቸውን፡ በሃይማኖትና በምግባር፡ለዚህ ጸጋ ላበቁ፡ ለሰው ልጆች ኹሉ ጭምር መኾኑን ነው።

እንግዴህ፡ መለኮታዊው እና ትስብእታዊው ልጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤ እግዚአብሔር እም ለተዋሓደቻት፡ ለሰብኣዊቷ እናቱ ድንግል ማርያም፡ በሰዎች ዘንድ፡ እንዲታወቅላት ያደረገው የማንነት ክብሯና ሥልጣኗ፡ ይህ ነው።

ታዲያ! የኹሉ ፈጣሪ የኾነው አምላክ፡ በሰብኣዊ አእምሮ፡ ሊታሰብ፤ በሰብኣዊ አንደበትም፡ ሊነገር፥ በሰብኣዊ ጥበብም፡ ሊገለጽ በማይቻል ቸርነቱ ያደረገውን፡ ይህን፡ የፍጹም ለጋሥነቱን ታላቅ ሥራ፤ ከዚህ የተነሣም፡ ራሱ ሰው፡ በእርሷ፡ በድንግል ማርያም ምክንያት፡ ያገኘውን፡ የመጨረሻውን ታላቅ ሥልጣንና ክብር እያደነቁ፤ እያመሰገኑም፡ ዝም ብለው በመኖር ፈንታ፡ ዓለማውያን ሰዎች፤ ድንግል ማርያም፡ ሥጋ የለበሰች ሰብኣዊት ፍጡር ብቻ መስላቸው፡ "አታማልድም!" የሚሉት፡ ይህ ዘይቤአቸው፡ ከቶ ምንድር ነው?

ይህንም እያሉ፡ በዚህ ዓለም፣ በምድር ላይ፡ እርስ በርሳቸውና በመካከላቸው የሚያካኺዱትን፡ የክፉዉን ቅንዓትና ምቀኝነት ግንዛቤ፡ ሳያፍሩና ሳይፈሩ፡ በመለኮት ልጁና በመለኮታዊት እናቱ ላይ ጭምር፡ እንዲህ መቀጠል ይገባቸው ነበርን? አይገባቸውም። የሚገባቸውማ፡ ድንግል ማርያምን በሚመለከት፡ እዚህ ላይ፡ የተብራራውን፡ ይህን፡ የእግዚአብሔርን እውነት ዐውቀውና ተረድተው፡ እየራሳቸውን፡ በሃይማኖታዊውና በምግባራዊው ንስሓ አስተካክለው፡ ወደቅዱሱ ኪዳን፡ የተዋሕዶ ኢትዮጵያዊነት መመለስ ብቻ ነው።

አዎን! የቃና ዘገሊላ ሠርግ በዓል፣ ከዚህ በላይ የታተተውን እንደያዘ ኾኖ፡ በተጨማሪ፡-

በአንድ ወገን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ቀድሞ፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ በመጀመሪያ፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በፍጥረተ-ዓለሙ የፍጻሜ ዘመን፡ በትስብእትነት [በሰውነት]፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ የወለደችውን፡ የእናቱን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡ እውነተኛ ማንነት፣

በሌላው ወገን ደግሞ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ቀድሞ፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ በመጀመሪያ፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በፍጥረተ-ዓለሙ የፍጻሜ ዘመን፡ በትስብእትነት [በሰውነት]፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከእግዚአብሔር አብ የወለደችውን፡ የልጁን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ እውነተኛ ማንነት፣ ኹለቱም በየበኩላቸው፡ አንዳቸው፡ የአንዳቸውን ያሳወቁበት ዐውድ መኾኑን መገንዘቡ ይጠቅማል።

ይህ፡ የቃና ዘገሊላ በዓል፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በጥር ፩ እና ፯ ቀኖች እንዲከበሩ ከተደረጉት፡ ከጥምቀትና ከቅድስት ሥላሴ በዓላት ቀጥሎ፡ በጥር ፲፪ ቀን፡ ሊከበር አስፈላጊ የኾነውም ያለበቂ ምክንያት አይደለም።

እግዚአብሔር አብ፡ ከደመና በተሰማ ድምፅ፣ እግዚአብሔር ወልድ፡ በእደ ዮሓንስ ሊጠመቅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል በቆመው፡ በኢየሱስ መሲሕ የትስብእት አካል፣ እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስም፡ ከሰማይ በወረደ ነጭ ርግብ አምሳል፥ መንበረ-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውም፡ እግዚአብሔር እም፡ ከመጥምቁ አጠገብ በነበረችው፡ በድንግል ማርያም ሰውነት ከተገለጡበት ከምስጢረ ጥምቀቱ ሥርዓት በኋላ መኾኑ በመረጋገጡ ነው።

*አዎን! የኢየሱስ መሲሕና የእናቱ፡ ድንግል ማርያም መለኮታዊነት፡ በተአምራት፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በይፋ የተገለጠው፡ በቃና ዘገሊላ ስለነበረ፡ ይህ፡ የቃና ዘገሊላ በዓል፡ ከጥምቀትና ከቅድስት ሥላሴ በዓላት ቀጥሎ መከበሩ፡ አግባብና ትክክል መኾኑ እሙን ነው።*

እግዚአብሔራችን ኢየሱስ መሲሕና ቅድስት እናቱ፡ እግዝእተብሔር ድንግል ማርያም በተገኙበት፡ በዚያ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ፡ ቅዱስ ሚካኤልም፡ እንዳልተለየ ስለሚታመን፡ የሊቀ-መላእክቱ በዓል፡ ከዚሁ፡ የቃና ዘገሊላ በዓል ጋራ፡ ዐብሮ እንዲከበር ማድረጉ፡ በእርግጥ፡ ተስማሚና ተገቢ ይኾናል።

እነዚህ ኹሉ ሥርዓቶች፡ አማናውያን፡ ማለትም፡ እውን የሚኾኑት፡ አምልኳችን፡ እንደእግዚአብሔር ቃል፡ "በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ" መፈጸሙን በየራሳችን ስናረጋግጥ ብቻ መኾኑ፡ ምንጊዜም መዘንጋት የለበትም።

## የቅዱሳን አማላጅነት ተረጋግጦ የተመሰከረበት ኹኔታና ከእኛ የሚጠበቀው፡ ሃይማኖታዊ ምግባር።

እግዚአብሔር፡ ስለቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ፡ በገሃድ ያሳየውን የመሰለ፡ መለኮታዊ የቸርነት ድርጊቱን፡ በብሉዩ ኪዳንና በአዲሱ ኪዳን ዘመናትም መፈጸሙ ታይቷል፤ ከእነዚህም መካከል፡ አንዳንዶቹን፡ እዚህ ላይ፡ እንደሚከተለው፡ በምሳሌነት ጠቅሰናቸዋል፦

፩ኛ፡ የብሉዩን ኪዳን በሚመለከት፡ በኢትዮጵያ ኖሮ፥ ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶና በእርሷ ብቻ ተወስኖ፡ ከእርሷ ልጆችን ከወለደ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ በዚህ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ፡ ወደግብፅ ልኮት፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ከባርነት፡ ነጻ ባወጣቸው፡ በቀድሞው ዕብራዊ፡ በሙሴ ላይ ስለደረሰው ገድል፡ የሚያስታውሰው ዜና መዋዕል ይገኛል።

አዎን! "የእስራኤል ልጆች" ይባሉ የነበሩት አይሁድ፡ የኢትዮጵያን ቀይ-ባሕር፡ በአባቶቻቸውና በእናቶቻቸው አምላክ ተአምራዊ ኃይል፡ ከተሻገሩ በኋላ፡ ሙሴ፡ ስለሚቀጥለው አካኼዳቸው፡ መለኮታዊዉን መመሪያ፡ ከፈጣሪው ለመቀበል፡ ወደደብረ-ሲና ወጥቶ፡ በሱባኤ፡ ለአርባ ቀናት ቢዘገይባቸው፡ ወንድሙን፡ አሮንን፡ ***"እንደአሕዛብ፡ ተሸክመን፡ በፊታችን የምናስቀድመው ጣዖትን ካላቆምህልን!"*** ብለው አስጨንቀው ላስቀረፁት የጥጃ ምስል፡ መስገዳቸውና መሠዋታቸው ይታወሳል።

እግዚአብሔርም፡ ይህን ግብራቸውን ዐውቆ፡ ለሙሴ፡- **"ርኢኩ ዘንተ ሕዝበ! ወናሁ፡ ዝንቱ ሕዝብ፡ ግዙፈ-ክሳድ። ወይእዜኒ፡ ኅድግኒ፡ እጥስዮሙ በመዓትየ! ወእሠይመከ፡ ላዕለ ሕዝብ ክቡድ፥ ወዓቢይ።**

"ይህን ሕዝብ አየሁት! እነሆም፡ አንገተ-ደንዳና ሕዝብ ነው። አኹንም፡ ይህን የመሰለ ጥፋት በሚያደርጉ የሰው ወገኖች ላይ የሚደርሰው የቅጣት ሥርዓት ተፈጽሞባቸው፡ ተንነው ሊያልቁ ነውና፡ ተዋቸው! አንተንም፡ እውነተኛና ታላቅ ለኾነ [ለኢትዮጵያ] ሕዝብ፡ መሪ አገልጋይ ትኾን ዘንድ እሾምሃለሁ።" ባለው ጊዜ፡ ሙሴ፡ ስለሕዝቡ፡ በአምላኩ ፊት ጸልዮ፣ እንዳማለደ፥ **"ወሰረየ እግዚአብሔር፡ በእንተ እኪት፡ ዘይቤ ይግበር ላዕለ ሕዝብ።**

"እግዚአብሔርም፡ በሕዝቡ ላይ፡ በጥፋታቸው ምክንያት፡ 'ይደርስባቸዋል!' ብሎ የተናገራት የቅጣት ሥርዓት፡ በምሕረቱ፡ እንድትቀርላቸው አደረገ።" በሚለው፡ የኦሪቱ ቃል መሠረት፡ ይኸው ሙሴ፡ ለበደለኞቹ፡ ለእስራኤል ልጆች፡ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዳስገኘ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ተረጋግጧል። (ዘጸአ. ፴፪፥ ፯-፲፬።)

፪ኛ፡ የአዲሱን ኪዳን በሚመለከት፡ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ የተናገራቸው ቃላት፡ እግዚአብሔር፡ በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው ለበቁት የሰው ልጆች፡ በሕይወተ-ሥጋም ሣሉ፣ በሕይወተ-ነፍስም እያሉ፡ ለሰጣቸው፡ የማማለድ ጸጋ፡ በቂ ማስረጃዎች ናቸው። ከእነዚህም መካከል፡ እንዲህ የሚሉትን፡ ለአብነት ያህል እንጠቅሳቸዋለን፡-

**"ዘኪያክሙ ተወክፈ፡ ኪያየ ተወክፈ፤ ወዘኪያየ ተወክፈ፡ ተወክፎ ለዘፈነወኒ። ዘተወክፈ ነቢየ፡ በስመ ነቢይ፣ ዕስበ ነቢይ ይነሥእ። ወዘተወክፈ ጻድቀ፡ በስመ ጻድቅ፡ ዕስበ ጻድቅ ይነሥእ። ወዘአስተየ፡ ለአሓዱ፡ እምእሉ ንኡሳን፡ ጽዋዐ ማይ ቈሪር ባሕቲቶ፡ በስመ ረድእየ፡ አማን እብለክሙ፡ ኢየኀጕል ዕስቦ። ...አማን! አማን! እብለክሙ፤ ዘየአምን ብየ፡ ግብረ፡ ዘአነ እገብር፣ ውእቱኒ ይገብር፤ ወዘየዓቢ እምኔሁ ይገብር።**

"እናንተን የሚቀበል፡ እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል፡ የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን፡ በነቢይ ስም የሚቀበል፤ የነቢይን ዋጋ ያገኛል። ጻድቅንም [በእግዚአብሔር የሚያምን፡ እውነተኛንም]፡ በጻድቅ ስም የሚቀበል፡ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል።

"ማንም፡ ከእነዚህ፡ ከታናናሾቼ፡ ለአንዱ፡ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃን ብቻ፡ በደቀ-መዝሙር ስም የሚያጠጣ፡ እውነት እላችኋለሁ፣ ዋጋውን አያጣም። ...እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ! በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" (ማቴ. ፲፥ ፵-፵፪። ዮሐ. ፲፩፥ ፲፪።)

እዚህ ላይ ግን፡ በብርቱ ልናስተውለውና ልንፈጽመው የሚገባን፡ አንድ ታላቅ፡ ሃይማኖታዊ ቍም-ነገር አለ፤ ያም ቍም-ነገር፡ እንዲህ በሚል አጭር ዐረፍተ-ነገር ተጠቃልሎ ሊገለጽ ይቻላል፦

"የእግዚአብሔር ወልድ፡ የኢየሱስ መሲሕ እናቱ የኾነችው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ሳይኾን፡ "**ያማልዱናል!**" ብለን፡ ዘወትር የምንማፀናቸው፡ የቅዱሳንና ቅዱሳት፡ ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፥ የቅዱሳን መላእክት ጭምር፡ "<u>የፈቃዳቸውና የፍላጎታቸው፥ የገድላቸውና የመሥዋዕትነታቸው፡ ዋና ዓላማና ግብ፡ ከቶ ምንድር ነው?" ብለን፡ በእውነተኛው መንፈስ ቅዱሳዊ አምልኳችን ተጠምደን ብንጠይቅ፡ የምናገኘው መልስ፡ እንዲህ የሚል ኾኖ እናገኘዋለን፦</u>

<u>"እኛ ወገኖቻቸው፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ በእነርሱ ምልጃ ብቻ ተማምነን፡ የዚህ ዓለም፡ ሥጋዊ ኑሮአችን፡ በሞት እስኪያበቃ እንድንቀጥል ሳይኾን፡ እያንዳንዳችን፡ እነርሱ ለደረሱበትና ለተቀዳጁት ጸጋና በረከት፥ ማዕርግና ክብር፡ እየራሳችንን አብቅተንላቸው እንድንገኝ ነው።"</u>

# አስተርእዮ ማርያም።

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወደአርያም ያደረገችው፡ የፍልሰቷ መታሰቢያ በዓል፡ በየዓመቱ የሚውለው፡ ጥር ፳፩ ቀን ነው። እርሱም፡ "**አስተርእዮ ማርያም**" በሚል ስያሜ ይጠራል፤ በዓሉ፡ እንዲህ ባለ ስያሜ ሊጠራ ያስፈለገበትን ምክንያት ለማብራራት፡ ይኸው ምክንያት፡ **ታላላቅ የኾኑ** አምላካውያት ምሥጢራት የተከሠቱበትን ኹኔታዎች ያካተተ በመኾኑ፡ ሰፊና ጥልቅ ቢኾንም፡ በጥቂቱ ሳንገልጸው አናልፍም።

## "አስተርእዮ" ምን ማለት ነው?
## መልእክቱስ፡ ምንድር ነው"

በመጀመሪያ ነገር፡ "አስተርአየ" የሚለው፡ የግእዙ ቃል፡ "አሳየ፤ ገለጠ፤ አበራ፤ ነገረ፤ አስተማረ፤ አሳወቀ፤ አስረዳ" ማለት ነው። "አስተርእዮ" የሚለውም ቃል፡ ከዚሁ የተገኘ ሲኾን፡ "የገለጠበት፥ የተገለጠበት፤ ያሳየበት፥ የታየበት፤" ማለት ነው። ምኑን የገለጠበትና ያሳየበት? ማንነቱንና ምንነቱን ነዋ! ምን ኾኖ፥ እንዴትስ ኾኖ የተገለጠበትና የታየበት? ይህ ኾኖ፥ እንዲህም ኾኖ የተገለጠውና የታየው፡ እርሱ፡ ማነው? "እውነትና መንፈስ የኾነው፡ እርሱ፡ የማይታየው፡ ፈጣሪና የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር፡ በገሃድ ሊገለጥና በግዘፍ ሊታይ፡ ሰው ኾነ! በሰውነት ተገልጦ ታየ!" ለማለት፡ ይህ ኹሉ መለኮታዊ ትንግርት የተፈጸመበት ወራት፡ "አስተርእዮ" ተባለ።

ይህ አስተርእዮት፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር፡ በሰውነት የመገለጡና የመታየቱ ምሥጢራዊ ትንግርት የተፈጸመበትን ኹኔታ፡ እስኪ፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል እናቅርበው! ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት አካሏና ባሕርይዋ፡ በተፈጠረችበት በእግዚአብሔራዊው መልኳ፥ በእርሱ በፈጣሪዋም፡ "**ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነች!**" በተባለችበት አምላካዊት ማንነቷ፡ ራሷን፡ ለዚያ ፍጹምነት አብቅታ ተገኘች። በዚህ ጊዜና ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡-

በቅድሚያ፡ ለሌላ ለማንም ፍጡር ተገልጦና ታይቶ ሊታወቅ ባልቻለ የአስተርእዮቱ ምሥጢር፡ ከፈጣሪ በኩል፡ ራሱ እግዚአብሔር፥ ከቅዱሳን መላእክቱ ወገን፥ ቅዱስ ገብርኤል፥ ከሰብአውያን ፍጡሮቹም በኩል፡ ራሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እኒህ ሦስቱ ብቻ ባወቁት ክሥተትና ርእዮት፡ የድኅነቱ ምሥራች በተነገረበት፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን፡ ፭ሺ፬፻፺፱ ዓመተ ኪዳን፡ እግዚአብሔር እም በተዋሓደቻት፡ በእርሷው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን፡ በትስብእትነት ተፀነሰ፤

ቀጥሎ፡ የአስተርእዮቱን አድማስ፡ በበለጠ በማስፋት፡ በፈጣሪ በኩል፡ ራሳቸው ቅድስት ሥላሴና በመንበረ ጸባዖቱ ዙርያ ያሉትን፥ በሱራፌልና በኪሩቤልም የታቀፉትን አርባዕቱ እንስሳን፥ ከቅዱሳን አንጋደ መላእክትም፡ ከነመንጎቻቸው፡ በሜዳ ሠፍረው በነበሩ እረኞች ዘንድ የታዩት፡ የሰማይ መላእክት፥ የምድር ሠራዊት ከኾኑት፡ ከሰው ወገኖች ደግሞ፡ እነቅዱስ ዮሴፍና ሕፃኑን ኢየሱስን ያሟሙቁት እንስሳት፥ እረኞቹም፡ ከነመንጎቻቸው፥ ከዚያም፡ እነሰብአ ሰገል ብቻ ባወቁት፡ የምሕረቱ ዓመት በባተበት፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ በሰውነት ተወለደ፤

እንዲህ፡ በፍጹም ሰውነት፡ እስካኹን፡ ለጥቂቶችና ለብዙዎች ብቻ የተገለጠውና የታየው እግዚአብሔር፡ አኹን ደግሞ፡ ይኸው፡ እውነተኛ ማንነቱና ምንነቱ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ በሙሉ፥ ለኹሉም፡ በይፋ ይታወቅ ዘንድ፡ በጥር፡ ፩ ቀን፥ ፴ ዓመተ ምሕረት፡-

ሰማዩ ተከፍቶና አባቱ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ፡ "**ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፡ ዘአፈቅር፡ ዘቦቱ ሠመርኩ!** ቀድሞ፡ በመጀመሪያ፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ በመጨረሻ፡ በሰውነት፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የወለድሁት፡ የምወድደው፥ በእርሱም ደስ የምሰኝበት ልጄ፡ ይህ ነው!" ብሎ ቃሉን በማሰማት፣

ቅድስት እናቱ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምም፡ በወንዙ አጠገብ ቆማ፡ የራሷንና "**ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!** ልጄ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!" ብላ የተናገረችለትን፡ የእርሱን፡ የልጇን ማንነትና ምንነት፡ በእናትነቷ በማረጋገጥ፣

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ "**ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ፤ ወርእየ መንፈሰ እግዚአብሔር፡ እንዘ ይወርድ፡ በአምሳለ ርግብ፤ ወነበረ ላዕሌሁ።** እነሆ! ሰማይ ተከፈተለት፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ፡ በርግብ አምሳል፡ ሲወርድ፥ በእርሱም ላይ ሲያርፍበት አየ!" እንደተባለ፡ ከሰማይ ወጥቶ በሚበርር ርግብ ተመስሎ ወርዶ፡ በላዩ በማረፍ፥

ራሱ አጥማቂው ዮሓንስም፡ "**ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፣ ዘየአትት፥ ወያሴስል ኃጢአተ ዓለም!** እነሆ፡ የዓለሙን ኃጢአት፡ ፈጽሞ የሚያስወግድ፣ የሚደመስስም፡ የእግዚአብሔር በግ!" ካለ በኋላ፡ **ወበውእቱ፡ ያጠምቀክሙ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት!** በመንፈስ ቅዱስ፥ በእሳትም የሚያጠምቃችሁ፡ እርሱ ነው!" ብሎ፡ ለደቀ መዛሙርቱ በማመልከት፡ ኹሉም፡ ስለማንነቱ መስክረውለት፥ በመጥምቁ ዮሓንስ እጅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። (ማቴ. ፫፥ ፲፩-፲፯። ዮሓ. ፩፥ ፳፱ እና ፴፯።)

በዚህ መልክና ይዘት፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን በኾነው ፅንሰቱ የተጀመረውና በመስከረም ፩ ቀን በኾነው ልደቱ የቀጠለው፥ ሲካኼድ ቆይቶም፡ በጥር ፩ ቀን በኾነው ጥምቀቱ ያበቃው፡ እግዚአብሔር፡ በሰውነት በመገለጥና በመታየት የፈጸመው የቸርነት ሥራው፡ እየታሰበ የሚከበርበት፡ በተለይ፡ ከጥር ፩ እስከ፳፰ ቀን፡ የሦስት ዕለታቷ "በዓለ ኢትዮጵያ" (የቀድሞዋ ጾመ ኢትዮጵያ = ጾመ ነነዌ) መግቢያ ድረስ ያለው ወራት፡ "**አስተርእዮ**" ተባለ።

# የቅድስት ድንግል ማርያም፡
# የአርያማዊ ፍልሰቷ ዜና።

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ቀድሞ፡ በሥነ ፍጥረት፥ ኋላም፡ በኢየሱስ መሲሕ ተገልጾ፡ ብዛታቸው፡ ሊቆጠር የማይቻል፡ መልካካም ቸርነቶችን፡ ላበረከተልን ፈጣሪያችን፡ ለእግዚአብሔር፡ እንደምናደርገው ኹሉ፥ "እግዝእተብሔራችንና እናታችን፥ ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን" ስለኾነችው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በየኅሊናችን የምናስበው፥ በአንደበታችን የምንናገረውና በየሕዋሳታችን የምንፈጽመውም ኹሉ፡ በየሕይወታችን ውስጥ፡ ዐብሮን ሕያው ኾኖ፡ ለዘወትር፡ ባለማቋረጥ የሚካኼድ እንጂ፡ በአንድ ቀን፥ ወይም፡ በአንድ ሳምንት፥ ወይም፡ በአንድ ወር፥ ወይም፡ በአንድ ዓመት ብቻ፡ የተወሰነ አይደለም።

አኹንም፡ እዚህ ላይ አቅርበን የምንጽፍላችሁ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ዜና መዋዕሏ፡ በተለይ፡ በአዲስ ኪዳኑ መጽሓፍ ውስጥ፡ ተመዝግቦ የሚነበበውን፥ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔራችን ኢየሱስ መሲሕ፡ እስካረገበትና መንፈስ ቅዱስ፡ በሓዋርያት ላይ፡ እስከወረደበት ቀን ድረስ ያለውን ሳይኾን፤ ከዚያ በኋላ፡ በዚያው መልክና ይዘት የቀጠለው፡ ምድራዊ ሕይወቷ፡ በ፷፬ ዓመታት ዕድሜዋ ካበቃበት፡ ከ"**ፍልሰቷ**"፡ ማለትም፡ **ሕያው በኾነው በአካለ ሥጋዋ፡ ከምድር፡ ወደሰማያዊቷ ገነት ተነጥቃ ከኼደችበት፡** ከጥር ፳፩ ቀን ተነሥተን፡ የመጨረሻ የኾነውን፡ ዜናዋን ብቻ ያካተተውን ዝክረ ነገር የምናስታውስበት ይኾናል፤ እርሱም፡ ይህንኑ፡ የመጀመሪያውን፡ የፍልሰቷን በዓል በምናከብርባት፡ በዚችው፡ በጥር ፳፩ ቀን፡ በሚነገረውና በሚሰማው፡ ከዚህ በታች በሠፈረው ቃል ተካትቶ ቀርቧል።

## "ፍልሰታ" ምንድር ነው?

"ፍልሰት"፥ ወይም፡ "ፍልሰታ" የሚባሉት አርእስት ቃላት፡ "ፈለሰ" (*'ለ' ሳይጠብቅ)* ከሚለው፡ "ከቦታ ወደቦታ መዛወርን"፡ ማለትም፡ "አንድ ሰው፡ ካለበት ቦታ ተነሥቶ፥ ወይም፡ መኖሪያውን ነቅሎ፡ ወደሌላ ኼደ!" የሚል ትርጕምን ከሚያመለክተው፡ ከግእዝ ዘር የተገኘ ዘይቤ ነው፤ በኢትዮጵያኛ፡ "ለ" ጠብቆ፡ "ፈ<u>ለ</u>ሰ" ያሰኛል።

ከዚህ የተነሣ፡ **የእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም ሕያው ሰውነት፡ ከምድር፡ ወደሰማያዊቷ ገነት የመወሰዱን ተአምር ለማስረዳት፡ "ፍልሰታ ለማርያም"** እንላለን።

የእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም ፍልሰት፡ እውን ኾኖ የታየውና ተፈጽሞ የተገኘው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ በዕለተ እሑድ ነው። አዎን! ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መነገር የጀመረው፡ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ተፈጽሞበት፡ እግዚአብሔር ወልድን ፀንሶ የወለደውንና ዐጥብቶ ያሳደገውን፡ ያን፡ የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን ሕያው ሰውነት፡ አይሁድ፡ እጅግ በከፋው አላዋቂነታቸውና ሰይጣናዊ አስተሳሰባቸው፡ የሚቻላቸው መስሏቸው፡ በእሳት አቃጥለው ሊገድሏት በሞከሩበት ጊዜ ነው።

ያም ጊዜ፡ በቅድስት እናቱ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ቀዳሚ ምሥዋዐ መድኃኒትነት፡ ለሰው ዘር የተገኘውን ዘለዓለማዊ ደኅንነት መሠረት አድርጎ፤ በይበልጥ፡ ለእነርሱ ዘለዓለማዊ ሰላም ሲል፡ በገዛ ራሱ የመስቀል ቤዛነት፡ ያን፡ የሰው ዘር ጠላት የኾነውን ዲያብሎስን አስወግዶ፥ በተለይ፡ እነዚሁኑ አይሁድን ጭምር፡ እንዲህ፡ ለመጨረሻው ድል ለማብቃት፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሥጋ መጥቶ፤ ያን ተልእኮውንም ፈጽሞ፡ ወደክብሩ በተመለሰው፡ በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት ላይ፡ አድርገውት የነበረውን፡ ያንኑ ግፍና ጭካኔያቸውን፡ አኹንም፡ በዚያ፡ በእርሷ፡ በድንግል ማርያም፡ መለኮታዊ ሰውነት ላይ ለመፈጸም ባሰቡበት፥ በማሰብም ብቻ ሳይወሰኑ፡ አዎን! ለማድረግም የሞከሩበት ነበር።

እነዚሁ አይሁድ ግን፡ በዚያን ጊዜ፡ አኹንም፡ ገና ያላወቁት፥ ሊያውቁትም ያልተቻላቸው፡ አንድ ታላቅ እውነታ ነበር። ይኸውም፡ በእነርሱ ዘንድ፡ እንደዕሩቅ ብእሲ [እንደተራ የእኔ-ብጤ ሰው] የታየችውን፥ እርሷን፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡ እንኳንስ በእሳት መቃጠል፤ ከዚያም ቢያልፍ፡ የሞት ጽዋን በመቅመስ ማለፍ ቀርቶ፡ አንዳች ጉዳት፡ የጨረፍታ ያህል እንኳ፡ ሊደርስባት፥ ወይም፡ ሊያገኛት፤ እንደማይታሰብ፡ አዎን! ገና አላወቁም።

ገና ከመጀመሪያው፡ በፍጹም ሃይማኖቷና ምግባሯ፡ ሰውነቷን ለአምላክነት በማብቃቷ፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻትን፥ የእግዚአብሔር አብ ሙኽሪት ኾና፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ አንድዬ ልጃቸውን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ በመለኮትነትም፥ በሰውነትም፡ ልትወልድለት የበቃችውን፡ የእርሷን፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ አካልና ባሕርይ፡ እንዴት፡ ክፋትና ኃጢኣት፥ ሞትና መቃብር፥ መበስበስና ሌላውም ዓይነት ሙስና፡ እንኳንስ ሊደርስበት፤ ሊቀርበውና ሊያስበውም እንኳ፡ እንዴት ይቻለዋል? ፈጽሞ እንደማይቻለው፡ አዎን! እነርሱ፡ ገና አላወቁም።

እንኳንስ እርሷ፡ ከላይ እንደተገለጠው፡ እግዝእተብሔር እም፥ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗ የታወቀላት ድንግል ማርያም ቀርታ፡ በእርሷ እና በልጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ በማመናቸው፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" ተብለው፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቁት ኹሉ እንኳ፡ በእርሷና በልጇ መሥዋዕትነትና ቤዛነት ምክንያት፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋቸው እያሉም፡ ከክፉትና ከኃጢኣት፥ ከሞትና ከመቃብር መበስበስ ሳይቀር፡ ነጻ ኾነው፡ ምንም ዓይነት ሙስናና ጉዳት በሌለበት፡ በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም፡ ቅድስቲቱን የትንሣኤ ሕይወት እንደሚኖሩ፡ አዎን! ገና አላወቁም።

በምድር ላይ፡ በትስብእትነት ተወጥኖ የተካኼደው፡ የእርሷ፡ መለኮታዊ ተልእኮ የተፈጸመው፡ እርሷን መስላ የተገኘች፡ ሰብኣዊት ድንግልን በመዋሓድ፡ በዚያች ድንግል ማሕፀን፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ እግዚአብሔር ወልድን ፀንሳ በመውለድ፡ "**ብኪ ድኅነ ዓለም!** ዓለም፡ በአንቺ ዳነ!" የተባለችበትን፥ ታላቁና የመጨረሻው፡ መለኮታዊና ዘለዓለማዊ ዓላማ የኾነውን፡ **ፍጹም ድኅነትን** [**ፍጹም መዳንን**] በማስገኘት መኾኑን፡ ገና አላወቁም።

አዎን! በምድር ላይ፡ በትስብእትነት ተወጥኖ የተካኼደው፡ የእርሱ የልጇ የወዳጇ የኢየሱስ መሲሕ፡ መለኮታዊ ተልእኮ የተፈጸመው ደግሞ፡ መልካሙን ሰብኣዊ ፍጥረተ-ዓለም፡ በክፋቱ ጠንቅ እያመሰ፡ ይኸው ሰብኣዊው የፍጥረት ወገን፡ እርስ በእርሱ፡ ያለማቋረጥ በሚያካኺደው የጦርነት ዕልቂት፡ ሲጠፋፋ እንዲኖር በሚያደርገው፡ በዲያብሎስ የክፋት ኃይል ላይ፡ ይኸው ልጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በፍቅሩ ሥጋዊ ፋሲካነትና በምሕረቱ ደማዊት ቤዛነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ድልን በመጐናጸፉ፡ "**ወበወልድኪ፡ ኮነ ሰላም!** በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!" የተባለበትን፥ ታላቁና የመጨረሻው፡ መለኮታዊና ዘለዓለማዊ ዓላማ የኾነውን፡ **ፍጹም ሰላምን** በማስገኘት መኾኑን፡ ገና አላወቁም።

እርሷማ፡ እነዚያ ክፉዎቹ አይሁድ፡ በእርሷ ሰውነት ላይ ሊያደርጉ ያሰቡትን፥ አስበውም አልቀረ፡ የቃጡትን፡ ያን ጉዳት ሊያደርሱ እንደማይቻላቸው፡ በመለኮታዊው ኃይሏ፡ እንዲስሰማቸው አድርጋ፡ አሳወቀቻቸው። እንዲስሰማቸውና እንዲታወቃቸው ያደረገችውም፡ በቅዱሳት መላእክት ተነጥቃና ታጅባ፡ በይባቤ፡ ወደሰማያዊቷ ገነት በመፍለሷ ነበር።

*አዎን! "መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ" እና "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" የኾነችው፥ እኛ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆቿም፡ እንዲሁ እያልን የምንጠራት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንዲህ፡ በመላእክት ተነጥቃና ታጅባ፡ በይባቤ፡ ወደሰማያዊቷ ገነት ከፈለሰችባት፤ ከዚያን ዕለት አንሥቶም፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡* ***"ፍልሰታ-ለማርያም"*** *በሚል ስያሜ በምትታወቀው፡ በጥር ፳፩ ቀን፡ በዕለተ እሑድ፡ ስለተፈጸመውና ስለታየው፡ ስለዚሁ መለኮታዊ ትንግርት፡ የኾነውን ደግሞ፡ እስኪ እንስማ!*

*"ወልደ አብ ፡ ወልደ ማርያም"፡ "የአብ ልጅ ፡ የማርያም ልጅ" የኾነውና የተባለው፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመለኮትና የትስብእት ወላጆቹ ከኾኑት፡ ከእግዚአብሔር አብ አባቱ እና ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እናቱ፡ እንዲህ ተወልዶ፥ እርሷ፡ ቅድስት እናቱም፡ በመስቀሉ ሥር ሳይቀር በመቆም፡ ምንጊዜም ሳትለየው፡ ዲያብሎስንና የዲያብሎስ የክፋት ሠራዊት የኾኑትን፡ ርኵሳን መናፍስት፣ የእነርሱ ግብረ ዐበሮች የኾኑትን፡ የሰው ወገኖች ጭምር፡ በእናቱ ቀዳሚ መሥዋዕትነትና በራሱ የመጨረሻ ቤዛነት በተገለጠ የፍቅር ኃይል፡ ከ፴፫ ዓመታት በላይ ለኾነ ዕድሜ በመዋጋት፡ በፍጻሜው፡ ይኸው፡ ኹሉንም፡ በድል አድራጊነት አሸንፎ፡ ከምድረ ገጽ አስወገደ።*

*ነፍሳዊዉንና ሥጋዊዉን፥ መንፈሳዊዉንም የድል አድራጊነት መሣሪያውንም፡ ለቅዱሳንና ለቅዱሳት ሓዋርያቱ፥ ላመኑበት ተከታዮቹም ኹሉ፡ ካስረከባቸው በኋላ፡ ሕይወቱ በኾነው፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ ለዐሥር ቀን ቆይቶ፡ ራሱ እስኪመለስ ድረስ፡ እርሷ፡ እናቱ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ በመካከላቸው ባለችበት ጉባኤ ተሰባስበው ሣሉ፡ በዓይናቸው እያዩት፡ ወደሰማይ ዐረገ።*

*ባረገ፡ በዐሥረኛው ቀን፡ አኹንም፡ እርሷ፡ እናቱ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ በእኒሁ ሓዋርያቱና ባመኑበት ተከታዮቹ መካከል ባለችበት ጉባኤ ተሰባስበው እያሉ፡* ***"አንትሙሰ ትጠመቁ፡ በመንፈስ ቅዱስ!*** *እናንተ ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ!" ብሎ የሰጣቸውን፡ የተስፋ ቃሉን በመፈጸም፡ በኹሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ ኾኖ ተመልሶ ወረደባቸው፤ ተዋሓዳቸውም። (የሓዋ. ፩፥ ፬-፰። ፪፥ ፩-፬።)*

ከዚህ በኋላ፡ እርሷ፡ እናቱ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዋና ማእከላቸውና ሰብሳቢያቸው በመኾኗ፡ የእርሷና የእርሱ የኾነችውን፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን ምሥራች፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ ለማዳረስ፡ እኒሁ ሓዋርያቱና ያመኑበት ተከታዮቹ፡ በየአህጉሩ ተበታተኑ። ተልእኳቸውን እየፈጸሙ ሲመለሱም፡ በእርሷው ዙሪያ እየተሰበሰቡ፡ ተልእኳቸውን ሲያስፋፉ፡ **ለዐሥራ አራት** ዓመታት ያህል ዐብረዋት ኖሩ።

መቸም፡ አይሁድ፡ ኢትዮጵያዊው መሲሕ ኢየሱስ፡ በሥጋውና በደሙ የዋጃትና ዐትሞ ያጸናት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እየተስፋፋች የመኼዷን ትንግርት እያዩ፡ ዝም ብለው መቀጠልን፡ ሊቋቋሙትና ሊበግሩት የማይቻላቸው፡ የቍስል ላይ ቍስል ጦር ኾነባቸው። እንዲያውም፡ ይህ ኹኔታ፡ በእነርሱ ዘንድ፡ "አባታችን" በሚሉት፡ በአብርሃም ምክንያት፡ የቃል ኪዳን አምላካቸው የኾነውን፡ ቸሩ ፈጣሪያቸውን ካወቁበት ጊዜ አንሥተው፡ የግብር አባታቸው በኾነው በዲያብሎስ ምክንያት፡ በቃል-ኪዳን አፍራሽነታቸውና በአምልኮ አመንዝራነታቸው፣ በክፋታቸውና በክህደታቸው፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪያቸው ጋር፡ ሲቋሰሉበት የኖሩበት፡ የልበ-ደንዳናነት ዓመፃቸው፡ ጽኑ የቂም በቀል ነበልባላዊ እሳትን፡ በውስጣቸው ኮሰተረባቸው።

"ክርስቲያን ነኝ!" የሚለውን ወገን ጨምሮ፡ "ሃይማኖተኞች ነን!" እንደሚሉት፡ እንደዛሬዎቹ የዓለም ሕዝብ ክፍሎች ኹሉ፡ እነዚሁ አይሁድም፡ ለዚህ ሥጋታቸው፡ ማረጋገጫ፥ ይልቁንም፡ ለሓሳዊው ህልውናቸው፡ ጠንቅ፥ ለሰላማቸው፡ የማሰናከያ ዐለትና ለመጥፋታቸውም ምክንያት ኾና የተጋረጠችባቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ ኢትዮጵያዋ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን፡ ልጇን ወዳጇን፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ለመስቀል ሥቃይና ሞት ያበቃው፡ ያው፡ የአባታቸው የዲያብሎስ መንፈስ በተጠናወተው፡ በዚያው፡ በቀናተኛው ዓይናቸው አትኩረው ተመለከቱ።

በዚህ ጊዜ፡ እርሷን ለማስወገድ የሚያመቻቸውን ዘዴ ሲፈልጉ፡ ቀደም ብለው፡ በልጇ፡ በወዳጇ በኢየሱስ መሲሕ ላይ የተጠቀሙበት ግፍ፡ በቀላሉና በቅርብ ተከሠተላቸው። ስለዚህ፡ አኹንም፡ ያንኑ ዘዴ፡ በእርሷ፡ በእናቲቱም ላይ ሊፈጽሙ ይዘጋጁ ጀመር።

ያን ክፉ ዕቅዳቸውን፥ ይልቁንም፡ ይህችው፡ እመ-እግዚአብሔር ጸባዖት [የአሸናፊው እግዚአብሔር እናት]፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በ፷፬ (ስድሳ አራት) ዓመቷ፡ ወደሰማያዊቷ ገነት የምትፈልስበት ጊዜ መድረሱን፡ አስቀድሞ ያወቀው መንፈስ ቅዱስ፡ ይህንኑ፡ እኩይ ውጥናቸውን፡ በሥራ ላይ ከማዋላቸው በፊት፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ ፴፰ ዓመተ ምሕረት፡ በሕይወተ ሥጋዋ እንዳለች፡ ወደሰማይ እንድትነጠቅ አደረገ።

አይሁድ፡ የሚቻላቸው መስሏቸው፡ ያን፡ የእግዚአብሔር እም፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ሕያው ሰውነት፡ በእሳት አቃጥለው ሊገድሏት በሞከሩበት ጊዜ፡ እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ፡ እነዚሁ አይሁድ፡ በእርሷ ሰውነት ላይ ሊያደርጉ ያሰቡትን፥ አስበውም አልቀረ፡ የቃጡትን፡ ያን ጉዳት ሊያደርሱ እንደማይቻላቸው፡ በመለኮታዊው ኃይሏ፡ እንዲሰማቸውና እንዲታወቃቸው አድርጋ፡ አሳየቻቸው። ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡-

ያ ጊዜ፡ ሐዋርያት፡ ከየሀገረ ስብከታቸው መጥተው፥ በእናታቸው ቅድስት ድንግል ማርያም ዙርያም ተሰባስበው፡ እንደተለመደው፡ ሐዋርያዊት ተልእኳቸው ስለኾነችው፡ **ስለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ሲነጋገሩ የሰነበቱበት ነው።

ወደየሀገረ ስብከታቸው ለመመለስ፡ ከመለያየታቸው በፊት፡ በኹለንተናዊ ደስታና ሓሤት ኾነው ለመሰነባበት፡ እኒሁ ሐዋርያት፡ እናታቸውን ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ስለገናና ክብሯ፡ አጎበር ባለው መከዳ ላይ አስቀምጠውና ተሸክመው፡ እርሷና እነርሱም፡ ወዳስለመዷትና ወደሚያዘወትሯት፡ ወደጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ፡ ይዘዋት ሲኼዱ፡ አይሁድ አዩ።

ይህች ጌቴሴማኒ፡ ቀድሞ፡ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለብሕትውና የሚያዘወትራት፥ የመጨረሻዋን የሕማማተ መስቀል ጽዋ ሞቱን ገፈት የቀመሰባት፡ የዕለተ ዓርብ ዋዜማ በኾነችው፡ "ምሴተ ሐሙስ" በተባለችውም፡ የሐሙስ ምሽትና ማታ፡ እኒሁኑ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ፡ ወደእርሷ ኼዶባት፡ ከእነርሱ ጋር የተሰነባበተባት፡ ያችው፡ ያትክልት ቦታ ናት።

አይሁድ፡ ይህ ዓይነቱ፡ የመንፈስ ቅዱስ ትዕይንት፡ ሲካኼድ ሲያዩ፡ ስለአምላክ እናት፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያም፡ የታሰባቸው፡ መለኮታዊው ክብሯ ሳይኾን፡ ሰብኣዊው ውርደቷ ኾነ! የታያቸውም፡ ሕያው ህልውናዋ ሳይኾን፡ የሥቃይ ሞቷ ኾነ!

ከዚህ የተነሣ፡ ያ፡ በዝማሬ ድምፅ የተመላው የደስታ ዐጀብ፡ በዓመፅና በባዕድ አምልኮ ጩኸት ለደነቆረው፡ ለእነርሱ ጆሮ፡ ሙሾና የልቅሶ ዋይታ ኾነባቸው፤ በቅንዓት ጨለማ ለታወረው ዓይናቸውም፡ የቀብር ጕዞ ኾኖ ታያቸው፤ መቸም፡ እነርሱን፡ የሃይማኖት ክህደትና የምግባር ክፋት፡ መለያ ምልክቶቹ በኾኑለት፡ በፀረ-እግዚአብሔርነት ባሕርያቸው አማካይነት፡ አንዴ፡ አባታቸው ዲያብሎስ ተጠናውቷቸዋልና።

እንዲህ፡ እንዲሰማቸውና እንዲታያቸው ያደረገው፡ ይኸው ሓሳዊና ምትሓታዊ መሪያቸው፡ በምትሓቱ፡ ለእነዚሁ አይሁድ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ነፍሷ፡ ከሥጋዋ ተለይታ፣ ሓዋርያት፡ ሊቀብሩዋት፡ ሬሳዋን፡ በአስከሬን ተሸክመው፡ ወደመካነ መቃብር የሚኼዱ አስመስሎ አቅርቦላቸው ኖሮአል። ስለዚህ፡ እንደልማዳቸው፡ እነዚያው፡ ልጇን፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ሰቅለው የገደሉት አይሁድ፡ "ቀድሞ፡ ልጇን፡ 'ተነሣ! ዐረገ!' እያሉ፡ ሲያውኩን ይኖራሉ፤ ዛሬ ደግሞ፡ እርሷን፡ 'ተነሣች! ዐረገች!' እያሉ፡ ሊያውኩን አይደለምን? ኑ! በእሳት እናቃጥላት!" ብለው ተነሡ። ከመካከላቸውም፡ "ታውፋንያ" የሚባል አይሁዳዊ፡ ተራምዶ፡ እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የተቀመጠችበትን፡ የመከዳውን ሸንኰር ጨበጠው። ወዲያው፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ኹለቱንም እጆቹን ቀጣው [ቆረጠው]። እጆቹም፡ በሸንኰሩ ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ።

ታውፋንያ፡ ሳያስበው፡ ድንገት በደረሰበት፡ በዚህ ጽኑ መቅሠፍት፡ እጅግ ተደናግጦ፡ እዚያው በወደቀበት፡ በኢየሱስ መሲሕ አመነ! "የእውነተኛው የእግዚአብሔር ልጅ፡ የኢየሱስ መሲሕ እናት፡ በእውነት፡ አንቺ፡ ድንግል ማርያም ነሽ! ስለዚህ፡ እኔን፡ በደለኛውን፡ ይቅር ትዪኝ ዘንድ፡ እለምንሻለሁ!" ሲል፡ በልቅሶና በእንባ፡ ወደእናታችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ባቀረበው መማጠን፥ በሓዋርያትም ጸሎት፡ እጆቹ፡ ወደነበሩበት አካሉ ተመልሰውለት፡ ደኅና ኾነ! ምስጋናውንም፡ ከታላቅ ደስታ ጋር ገለጸ።

ከዚህ በኋላ፡ እርሷ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመላእክት ተከልላና ተጠብቃ፥ በልዩ መለኮታዊ ይባቤ፡ ወደሰማያዊቷ ገነት ተነጥቃ ተወሰደች።

"መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ" እና "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" የኾነችው፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻት፡ ድንግል ማርያም፡ እንዲህ፡ በመላእክት ታጅባ፡ በይባቤ፡ ወደ ሰማያዊቷ ገነት በመነጠቅ፡ በኼደችበት የፍልሰቷ ጊዜ፡ የኾነውን ደግሞ እንስማ!

ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡- ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ፡ ቅዱስ ሥጋውን በግርፋት እየተለተለና ክቡር ደሙንም በውጊት እያፈሰሰ፡ የቤዛነቱን ተልእኮ እየፈጸመ ባለበት ሰዓት፡ ከመስቀሉና ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም አጠገብ ሳይለይ፡ የዚሁ ልጇን ኑዛዜያዊ የአደራ ቃል ተቀብሎ፡ እርሷን፡ እናት፥ ራሱንም፡ ልጇ አድርጎ፡ ይጠብቃት የነበረው፡ ወንጌላዊው ዮሓንስ፡ አኹንም፡ ዐብሯት ኾኖ፡ ይህንኑ የፍልሰቷን እውነታ ለማየት የበቃ ኾነ።

አዎን! እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ቅዱሳን መላእክት፡ በደመና ነጥቀውና ዐጅበው፡ በታላቅ ይባቤ፡ ከምድር ወደሰማያዊቷ ገነት በወሰዷት ጊዜ፡ ሓዋርያውንና ወንጌላዊውን ቅዱስ ዮሓንስን፡ ከብቅዓቱ የተነሣ፡ ዐብሩዋት እንዲገኝ አድርገውት ነበርና፡ በሰማያዊቷ ገነት፡ በዕፀ ሕይወት [የሕይወት ዛፍ] ቦታዋ ማረፏን አይቶ፡ ወደምድር ተመለሰ።

ተመልሶ፡ በቀሩት ሓዋርያት መካከል በተገኘ ጊዜ፡ በጕጕት፡ ዙሪያውን ከብበው፡ "እናታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እንደምን ኾነች?" ብለው ጠየቁት።

ወንጌላዊው ዮሓንስም፡ "እርሷ፡ እናታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምማ፡ **በገነት፡ በዕፀ ሕይወት ቦታዋ ዐርፋለች!**" ብሎ፡ ዜናውን በማሰማት፡ የምሥራቹን ቃል አደረሰላቸው።

ሌሎቹ ሓዋርያት፡ ይህን፡ ከወንድማቸው፡ ከሓዋርያው ዮሓንስ አንደበት የሰሙትን፡ የእናታቸውን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን የሕያው ፍልሰታዋን፡ ታላቅና ተአምራዊ ምሥራች፡ እነርሱም፡ በዓይናቸው ባለማየታቸው አዝነው፡ "ወንድማችን ዮሓንስ፡ ዐብሮሽ በመገኘት፡ ለመሳተፍ የታደለበትን ይህን አርያማዊ ክብርሽን፡ እኛንም ለማየት አብቂን!" በማለት፡ በሚቀጥለው፡ በነሓሴ ፩ ቀን፡ የኹለት ሳምንት ሱባዔን ጀመሩ። ይኼም ሱባዔያቸው፡ የነገሩን ኹሉ፡ እውነተኛ ምሥጢር እንዴት እንደገለጠላቸው፥ ፍሬያማውንም ምላሽ፡ እንዴት ማግኘት እንደቻሉ፡ በጊዜው እንመለከተዋለን።

*[**ፍሬ ዕፀ-ሕይወትን፡** የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ኢየሱስ መሲሕን ያስገኘችው፡ ድንግል ማርያም፡ ራሷ፡ ዕፀ-ሕይወት (የሕይወት ዛፍ) ስትኾን፡* "በገነት፡ በዕፀ ሕይወት ቦታዋ ዐርፋለች!" *የተባለበትን፡ እጅግ ጥልቅ የኾነውን፡ ይህን ምሥጢር፡ በአንክሮና በተመሥጦ እያስተዋሉ ይመለከቷል።]*

እንግዴህ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከምድር ወደሰማይ ያደረገችው፡ ያ፡ ቀዳማዊውና ኹለንተናዊው ሕያው ፍልሰቷ የተፈጸመው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ በዕለተ እሑድ ነው። አዎን! ይህ፡ የመጀመሪያው ፍልሰቷ ነው።

# በዓለ ኢትዮጵያ።

<u>በዓለ-ኢትዮጵያ፡ ከጥር ፳፰ እስከ፴ ቀን፤</u> ባሉት ሦስት ዕለታት ይከበራል። ይህም በዓል፡ ወሮቿዋ እና ቀኖቿ፡ በየዓመቱ ይለዋወጡ በነበረችው፥ ከሰኞ እስከረቡዕ ያሉት፡ ተከታታይ ዕለታቷ ግን ሳይለዋወጡ፡ ትፈጸም የነበረችው፡ የቀድሞዋ፡ "ጾመ-ነነዌ"፥ የኋለኛዋም፡ "ጾመ-ኢትዮጵያ" ትባል በነበረችው መደበኛ ጊዜ፡ በ፲፫ኛው መለኮታዊ ዐዋጅ፡ **"በዓለ-ኢትዮጵያ"** በሚል ስያሜና ሥርዓት ተተክቶ የሚከበረው ነው።

በዚያ መለኮታዊ ዐዋጅ እንደተገለጸው፡ ይህ መደበኛ፡ ዓመታዊ የጾም ጊዜ፡-

-በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ቅርንጫፍ በኾነችው፡ ዛሬ፡ ራሷን፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን" ብላ በምትጠራው፡ የመነኮሳት ድርጅት፡ ቀድሞ፡ ለዝንተ-ዓለም፡ **"ጾመ-ነነዌ"** በሚል ስያሜ፡ ስትጾም የኖረችው ናት።

-ከዚህ በኋላ፡ በመካከሉ፡ የቅዱሱ ኪዳን ውለታውን አፍራሽ የኾነውን፤ ይህን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን፡ የዚህን ዘመን፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ አመንዝሪና ክፉ ትውልድ ሊቀጣ፡ የፍርድ ሠይፍን ታጥቆ የተላከው ደርግ፡ ከተነሣበት፡ ከሺ፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ፡ ዘለዓለማዊው ህልውናዋ ሊነካ በማይቻለው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ የቅዱሱ ኪዳን አገልግሎታቸውን በቀጠሉት፡ በዛሬዎቹ፡ ታማኞች ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ ይህችው ጾም፡ **"ጾመ-ኢትዮጵያ"** ተብላ፡ ለአርባ ዓመታት፡ በሱባኤ ምሕላ ስትጾም ቆየች።

-ቀጥሎ፡ ይህችው፡ የአርባ ዓመታት የሱባኤ ጾምና የምሕላ ጸሎት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የሰማዩ አባታቸውና የሰማዩዋ እናታቸው ከኾኑት፡ ከእግዚአብሔር አብወእም ፊት ደርሳ፡ የኪዳነ-ምሕረት ቸርነታቸውን ጸጋ ስላስገኘች፤

በቅድሚያ፡ ደርግ፡ የቅጣትና የጥፋት ተልእኮውን እንዲያበቃ ወስነው፡ ከሥልጣን እንዲወገድ፤

በማስከተልም፡ በእርሱ፡ በደርግ የሥልጣን ወንበር ላይ እንዲተኩ የተላኩት፡ የአኹኖቹ መሪዎች፡ በታጠቁት ሠይፍ፡ በገሃድ መሥራት እስኪጀምሩ ድረስ፡ በዚችው፡ በርስተ-ጉልት ምድራቸውና በቃል-ኪዳን ሕዝባቸው ላይ፡ በታወቁት ተፃራሪዎች ረቂቅ ተንኰል፡ ሊካኼድ ታቅዶ ከነበረው ሰይጣናዊ ጥቃት፡ አንዳች ጥፋትና ዕልቂት እንዳይደርስ ያደረጉበትን መለኮታዊ ጥበቃ፡ ኹላችሁም የምታዘክሩትና የምትመሰክሩት ነው።

ይኸውም፦ ፩ኛ. Communism [ኮሚዩኒዝም] በሚባለው፡ የ"እግዚአብሔር የለም!" የምሥራቃውያን ባዕዳን፡ ሰይጣናዊ ፍልስፍና እየተመራ፡ የኃይልና የግፍ፥ የጭካኔና የጭቆና፥ የግድያና የጥፋት፥ የቅጣትና የመቅሠፍት አገዛዙን፡ ለ፲፯ ዓመት ሲያካኼድ የቆየው፡ "ደርግ" የተባለው፡ አምባገነንና ግዙፍ ወታደራዊ ድርጅት፡ በተቃዋሚው፡ ጦር መሣሪያ ብልጫነትና በሠራዊት ብዛት ሳይኾን፡ በፍቱኑ መለኮታዊ የቅዱሱ ኪዳን ጸጋና እውነት ተወግዶ፡ በዚያው፡ የደርግ በኾነው፣ ነገር ግን፡ Democracy [ዲሞክራሲ] በሚባለው፡ በምዕራባውያን ባዕዳን መሠሪና ረቂቅ "የከፋፍለህና የለያይተህ" አመራርና አገዛዝ ፍልስፍና በተመሠረተው፡ አንጃ በተተካ ጊዜ፡ ተፈጥሮ በነበረው መንግሥት-አልባ በመሰለው ክፍተት ውስጥ፡ ቀደም ብሎ፡ በአብዮትና በጦርነት ምክንያት፡ በመላዋ አገር፡ ያለሕግና ያለፍርድ፡ በእልፍ-አእላፋት ላይ ከተፈጸመው የግፍ እስራትና ሥቃይ፥ ግርፋትና ግድያ የተነሣ፡ በሕዝቡ መካከል፡ በደመኛነትና በቂም በቀል ቁርሾ፡ ሊደርስ ይችል የነበረው፡ ታላቅ የደም መፋሰስና የእርስ በርስ ዕልቂት፡ ታግዶ እንዲያልፍ የተደረገው፡ የቅዱሱ ኪዳን ባለቤት በኾነችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፣ የእርሷ መሪዎቿ በኾኑት፡ በእግዝእተብሔራችን እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔራችን ወልድ ኢየሱስ መሲሕ አይደለምን? አዎን! ነው። ታዲያ! በማን መሰላችሁ!? ለመኾኑ፡ ይህን እውነታ የምታውቁ፡ ስንቶች ናችሁ?

፪ኛ፣ በዚያኑ ጊዜ፡ መላውን፡ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ፣ ከነንብረቱ፣ ከቅዱሳት መካናቱ ጋር ጭምር፣ በአጠቃላይ፡ የኖረውንና "አለ!" የሚባለውን፡ ሕያዉንና በድኑን ቅርስ፡ እንዳለ፡ ጨርሶ በመደምሰስ፡ መናገሻ ከተማዋን፡ ባዶ አድርጎ፡ አዲስ የኾነ ከተማን፡ በዘመናዊ መልክ ለመመሥረትና በአዲስ ነዋሪዎች ለማቋቋም ሲባል፡ የሰይጣን ወገኖችና የባዕዳን መሣሪያዎች በኾኑ፣ ቂም-በቀልንም በተመሉ፡ ክፉዎች ሰዎች መሠሪነት፡ በምስጢራዊ ተንኮል ታስቦና ታቅዶ፡ በተግባር ላይ እንዲውል ተደርጎ የነበረው፡ በከተማይቱ፡ በውስጧ፥ በመካከሏና በዙሪያዋ ባሉት የጦር መሣሪያዎችና ፈንጂዎች ግምጃ ቤቶች፥ በነዳጅ ዘይት ጋኖችና ማከማቻዎች ላይ፡ "ኾን" ተብሎ፡ በዚያው ሰሞን እንዲፈነዳ፡ ተነጣጥሮና ተተርኵሶ የነበረው የእሳት ገሞራ፡ ሊቀጣጠል እንዳይችል ተደርጎ፡ የተጠበቀውን አሠቃቂ ዕልቂት ሳያደርስ ሊጠፋ የበቃው፡ አኹንም፡ በማን መሰላችሁ? **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**፣ የእርሷ መሪዎቿ በኾኑት፡ በእግዝእተብሔራችን እም፡ ድንግል ማርያም እና በእግዚአብሔራችን ወልድ ኢየሱስ መሲሕ አይደለምን? አዎን! ነው። ታዲያ! በማን መሰላችሁ!? ለመኾኑ፡ ይህን እውነታ የምታውቁ፡ ስንቶች ናችሁ?

እንግዴህ፡ የመላውን ዓለም፡ የሰው ዘር የክፋትና የጥፋት ግብር ተከትሎ፡ ይህ፡ 'ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚለው፡ የዛሬው ትውልድ፡ በ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ በይፋ ያወጀውን፡ የቃል ኪዳን አፍራሽነትና የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአቱን፡ ምክንያትና መነሻ በማድረግ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች የተጀመረችው፡ **የጾመ-ኢትዮጵያ ሱባኤ፡** በእነዚህ ኹሉ ትንግርቶች፡ በ፳፻፮ [በ፪ሺ፮] ዓ. ም. **ልክ፡ የአርባው ዓመት፡ ሲፈጸም፡ የቅጣቱ መከራ ዘመን አብቅቶ፡ እነሆ፡ የምሕረቱና የምሥራቹ ጊዜ የባተ** [የገባ] **መኾኑን የሚያበሥረው መለኮታዊው ዐዋጅ፡ ራሷ "ኢትዮጵያ" በኾነችው፡ በራሷ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ቃል እንደተነገረ፡ ኹላችሁም** የተገነዘባችሁት፡ የቅርብ ጊዜ እውነታ ነው።

ስለዚህ፡ በዚሁ፡ ከላይ በተጠቀሰው፡ በ፲፫ኛው መለኮታዊ ዐዋጅ፡ በተሰጠን መመሪያ መሠረት፡ እነዚህ ሦስት ዕለታት፡ በመላው ፍጥረተ-ዓለም፥ በተለይም፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በየዓመቱ፡ <u>**"በዓለ-ኢትዮጵያ"**</u> ተብለው፡ እንዳለፉት ዘመናት፡ <u>**ቋሚዎቹ የጥር ፳፰ እስከ፴ ቀኖቻቸው፡**</u> የሚለዋወጡ ሳይኾኑ፥ ዟሪ ዕለቶቻቸው፡ ሰኞ፥ ማግሰኞና ረቡዕ ግን፡ የሚለዋወጡ ኾነው፥ ጊዜያቸውም፡ የምሕላና የጾም ሳይኾን፡ በፍጹም የዝማሬና የማኅሌት ምስጋና፥ በታላቅ ኹለንተናዊ የሥጋ፥ የነፍስና የመንፈስ ሓሤት፥ በፋሲካ የአለባበስ ድምቀትና የድግሥ ሥርዓትም የምናከብራቸው ይኾናሉ።

በዚህ ረገድ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ በእኔ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምና በልጇ በወዳጇ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የዐዋጅ ቃል፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ በይፋ ተገልጣ፡ የዕውቀትና የእውነት፥ የቸርነትና የአገልግሎት በረከቷን፡ በቀጥታ፡ በእኛው አማካይነት፡ ለፍጡሮቿ ኹሉ ማዳረሷን ትቀጥላለች።

በአጠቃላይ፡ ከመለኮታዊዉና ትስብእታዊው የእናትና የልጅ ፅንሰት፥ እንዲሁም፡ አስተርእዮ [መገለጥ] እና የእናቲቱ ሰማያዊ ፍልሰት ምሥራች የተነሣ፡ በታኅሣሥ ፴ ቀን ከሚጾመው የአንዲት ዕለት ገሀድ [የጥምቀት ዋዜማ ጾም] በቀር፡ **ከታኅሣሥ ፩ እስከጥር ፴ ቀን ድረስ** ያሉትንና እነዚህን ተከታታይ የመታሰቢያ በዓላት ያካተቱትን፡ ዕለታት የምናከብራቸው፡ ያለጾም፡ በፋሲካ የሓሤት ሥርዓት መኾኑን እንዳንዘነጋው ያስፈልገናል።

# ኪዳነ-ምሕረት።

እግዚአብሔር ወልድ፡ "ኢየሱስ መሲሕ" ተብሎ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘው፡ የመጨረሻው፡ ዘለዓለማዊ የምሕረት ቃል-ኪዳን፡ "**ኪዳነ-ምሕረት**" ይባላል። የዓመቱም በዓል፡ የካቲት ፲፮ ቀን የሚውል ኾኖ፡ በታላቅ ኹለንተናዊ ስሜትና ሓሤት ይከበራል።

የመጀመሪያዎቹ አዳም እና ሔዋን፡ የፈጣሪያቸውን ፈቃድ መተላለፋቸው፡ በእየራሳቸውና የእነርሱን ፈለግ በተከተሉ ልጆቻቸው ላይ፡ የዲያብሎስን ገዢነት፥ የሓሰትን [የኃጢአትን] ቀንበርና የሞትን ፍዳ አመጣባቸው።

በየዘመናቱ፡ ለደጋጎች ልጆቻቸው የተሰጡት፡ አምላካውያት ቃል-ኪዳናትና የ፭ሺ፭፻ ዓመታት ንስሓቸው ግን፡ አስቀድሞ፡ "እግዝእተብሔር እም"ን፥ ቀጥሎም፡ "እግዚአብሔር ወልድ"ን፡ ከሰማየ-ሰማያት ልዕልናቸው፡ ወደምድር አውርዶ፡ ሰው እስከመኾን አደረሳቸው፤ መለኮታዊዉም ፈቃድ፡ የመጨረሻዎቹ አዳም እና ሔዋን በኾኑት፡ በኢየሱስ መሲሕ እና በድንግል ማርያም ስለተፈጸመ፡ ይህ፡ ፍቅርና ርኅራኄ፡ የሰው ልጆች፡ የእግዚአብሔር ልጆች የኾኑበትን፡ የመጨረሻውን ክብር አቀዳጃቸው፤ የኃጢአትን ስርየትና የትንሣኤ ሕይወትንም አስገኘላቸው።

ይህ፡ የልጅነት ጸጋ፥ ይህ፡ የስርየት ነጻነት፥ ይህ፡ የትንሣኤ ክብር፡ ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖር ዘንድ፡ በመለኮታዊ የምሕረት ቃል-ኪዳን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ታተመ።

ማኅተሙም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ የተዋሓደውና በመስቀል ላይ የሠዋው፥ ዛሬም፡ እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ በንስሓ ነጽተን፡ ከቅዳሴ ሥርዓተ-ጸሎት በኋላ፡ የምንቀበለው፡ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ነው።

በእርሷ፡ በእናቱ፡ በድንግል ማርያም፥ በእርሱ፡ በልጇም፡ በኢየሱስ መሲሕ መለኮትነትና ሰውነት የተዋሕዶ ምስጢር፡ ለፍጥረቱ ኹሉ፥ በተለይም፡ ለሰው ዘር የተገኘው፡ ይህ ኹሉ ጸጋና በረከት፡ "**ኪዳነ-ምሕረት**" ተብሎ፡ በየዓመቱ፡ በየካቲት ፲፮ ቀን፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በጥልቅ መንፈሳዊ ተመሥጦ ይከበራል።

# መፈጽም።

እንግዴህ፡ እንደመለኮታዊው የዐዋጅ ቃል፡ "በገዛ ፍላጎታችሁና ምርጫችሁ፡ እየራሳችሁን፡ **ወደኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ያቀረባችሁ፡ የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያ ልጆች ኪዳናውያንና ኪዳናውያት! ፈጽማችሁ ደስ ይበላችሁ!

በዚህ አንጻር፡ በገዛ ፍላጎታችሁና ምርጫችሁ፡ እየራሳችሁን፡ **ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ያራቃችሁ፡ ሰብኣውያንና ሰብኣውያት ፍጡሮች ደግሞ! ከዚህ የበለጠ የሚበረከትላችሁ፡ "ምን ምሥራችና ደስታ፥ ሰላምና ዕረፍት አለ!" ትላላችሁ? የለም። አዎን! ስለሌለ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ የቅጽበት ንስሓ እየመለሳችሁ፡ **ወደኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ቅረቡ!

ይህ ኹሉ፡ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተገለጠው፡ የእግዚአብሔር እውነታ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መልእክታትና መጻሕፍት፤ የጥያቄ ጦማራትና የመልስ ድርሳናት፤ የሃይማኖት ምንባባትና የዐዋጅ ቃላት ውስጥ ተካትቶ ይገኛልና፡ እነዚያን ዝግጅቶች መመልከቱ ይጠቅማል።

\+ \+ \+